ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 262 ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


## የሀገርን ዳር ድንበር ለመጠበቅ ተመራቂ መኮንኖች ከሕገ መንግሥትና ከሀገር ፍቅር የተቀዳ ዓላማ ሊኖራቸው እንደሚገባ ተገለጸ

- የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት 69ኛው የኢትዮጵያ ወታደራዊ አካዳሚ የምርቃት ሥነ ሥርዓት ተካሂዷል



ፎቶ - ኢዮብ ተፈሪ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የዛሬ ምክትል መቶ አለቃ ተመራቂ መኮንኖች የነገ ጀኔራሎች ሀገርን ላለማስደፈር ከሕገ መንግሥቱና ከሀገር ፍቅር የተቀዳ ዓላማ ሊኖራችሁ ይገባል ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አስታወቁ፡፡

በምርቃት ሥነሥርዓቱ ላይ የተገኙት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንደተናገሩት፤ ሁሉም ተመራቂ መኮንን የሀገሩን ዳር ድንበር ለመጠበቅ ከሕገ መንግሥትና ከሀገር ፍቅር የተቀዳ ዓላማ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ሀገሩን አብዝቶ የሚወድና ለዓላማው ዝንፍ የማይል በቀጣይነት ማደግን የሚያስብ መኮንን እንደምትሆኑ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

ለመነሻ የሚሆን እውቀት ከወታደራዊ አካዳሚው ያገኙት ተመራቂ መኮንኖቹ በቀጣይ በሚሠማሩበት ግንባር ሁሉ ከበላይ ኃላፊዎችና

የሀገርን ዳር ድንበር ለመጠበቅ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## በመኸር ግብርና 390 ሚሊዮን ኩንታል ለማምረት ታቅዷል

- 12 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሟል
- 6 ቢሊዮን ችግኝ ለአረንጓዴ አሻራ ተዘጋጅቷል



ፎቶ - ዳኜ አበራ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ለግብርና ሴክተሩ ትኩረት በመስጠቱ አበረታች ስኬቶች እየተመዘገቡ መሆኑን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡በመኸር ግብርና 390 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት መታቀዱን የግብርና ሚኒስቴር አስታውቋል።

የግብርና ሚኒስትር አቶ ኡመር ሁሴን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ በሰጠው ትኩረት አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ ነዉ።

መንግሥት ግብርናውን ከኋላቀር አስተራረስ ዘዴ ለማላቀቅ ሜካናይዝድ የሆኑ ግብርና መሣሪያዎች ያለቀረጥ ወደሀገር ውስጥ እንዲገቡ ድጋፍ አድርጓል። የሀገሪቱን ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በመኸር ግብርና ላይ ተጨማሪ የበጋ መስኖ ግብርና ላይ ትኩረት በማድረግ እየተሠራበት መሆኑን ገልጸዋል።

በዋናነትንም ዘንድሮ ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ግብዓቶችን ለማቅረብና ለማሰራጨት አመርቂ ዝግጅት መደረጉን አመልክተው፤ የ12 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሟል።የክልሎች ማዳበሪያ ማከማቻ ማዕከል ከደረሰው 8 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ አራት

በመኸር ግብርና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## "በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በሸኔ የተያዘ አንድም ቀበሌ የለም"

-የክልሉ የጸጥታ ቢሮ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በፊትም ሆነ በአሁን ወቅት በሸኔ ቁጥጥር ሥር የዋለ ወረዳም ሆነ ቀበሌ የለም ሲል የክልሉ የጸጥታ ቢሮ አስታወቀ፡፡ መንግሥት በአሸባሪ ቡድኑ ላይ የተሳካ ዘመቻ እያካሄደ ነው፡፡

የኦሮሚያ ክልል አስተዳደርና የጸጥታ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ኮሎኔል አበበ ገረሱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ አሸባሪው የሸኔ ቡድን በኦሮሚያ ክልል የተቆጣጠራቸው ቦታዎች እንዳሉ ቢነገርም ቡድኑ ከበፊትም ጀምሮ እስካሁን ድረስ የተቆጣጠረው ወረዳ፣ ቀበሌ አሊያም ምንም መንደር የለም፡፡ መንግሥት የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ በአሸባሪው የሸኔ ቡድን ላይ እየወሰደ ያለው ዘመቻም የተሳካ ሆኗል፡፡

የሽብር ቡድኑ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎችን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሯል ተብሎ ትክክለኛ ያልሆነ ወሬ ቢወራም አሸባሪው ሸኔ ሾልኮ ገብቶ ንጹሐንን ከመግደል ውጭ በፊትም ሆነ በአሁን ወቅት የተቆጣጠረው ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ ወይም መንደር እንደሌለ ኮሎኔል አበበ ገልጸዋል፡፡ በአጥፊው የሸኔ ቡድን ሳቢያ ሕዝቡ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ተስኖት እንደነበር አስታውሰው፤ በአሁን ወቅት በብዙ ቦታዎች ላይ ሥርዓት እንዲከበር መደረጉንም ነው ያስታወቁት፡፡

እንደ ኮሎኔል አበበ ገለጻ፤ አሸባሪው የሸኔ ቡድን የሃይማኖት ተቋማትን ጨምሮ፣ ትምህርት ቤቶችንና የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ያወደመ ፤ ከግድያ ባለፈ ሰዎችን ከነነፍሳቸው ያቃጠለና ወደ ገደል የከተተ ቡድን ነው፡፡ ሴቶችን በባሎቻቸው ፊት የደፈረ፤

"በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ሀገር እና ደጋግ ልቦች...
ገጽ 7

ተማሪዎች ነቃ፣ እናቶች እፎይ ያሉበት - የተማሪዎች ምግብ
ገጽ 9

ዜና

# “የድርቁ አደጋ የሰው ሕይወት ሳይነጥቅ ምላሽ እንደተሰጠ ሁሉ ለዋጋ ንረቱም ምላሽ ለመስጠት እየተሠራ ነው”

- አቶ ሙስጠፌ መሐመድ



አዲስ አበባ፤ “የድርቁ አደጋ የሰው ሕይወት ሳይነጥቅ ምላሽ እንደተሰጠ ሁሉ ለዋጋ ንረቱም ምላሽ ለመስጠት እየተሠራ ነው” ሲሉ የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ መሐመድ ተናገሩ።

ርዕሰ መስተዳድሩ የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በክልሉ እየታየ ያለውን የዋጋ ግሽበት በሀገራችን እና በዓለም እያስከተለ ያለውን የዋጋ ንረት ብቻውን ሊፈታው አይችልም ብለዋል።

ነገር ግን የክልሉ መንግሥት የድርቁ አደጋ የሰው ሕይወት መጥፋት ሳያስከትል ምላሽ እንደሰጠው ሁሉ፣ መንስኤው ዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ የሆነውን የዋጋ ንረት ለመቆጣጠር የተለያዩ ስትራቴጂዎችን እና እቅዶችን አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን መግለፃቸውን ከክልሉ መንግሥት ኮሙኒኬሽን ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

እንደ ርዕሰ መስተዳድሩ ገለፃ፥ የክልሉ መንግሥት ከወራት በፊት ከወሰዳቸው ስትራቴጂዎች መካከል ሕገ ወጥ የኮንትሮባንድ ንግድን መቆጣጠር፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላለው የኅብረተሰብ ክፍል ድጋፍ ማድረግ፣ የግብርና ምርታማነትን ማሳደግ ሲሆኑ፥ እነዚህ በጅምር ላይ ያሉ እንቅስቃሴዎች በመሆናቸው መጠናከር እና በፍጥነት መተግበር አለባቸው ነው ያሉት ።

በተጨማሪም መንግሥት የአገር ውስጥ በጀትና ተቋማዊ የገንዘብ ድጋፍን ተጠቅሞ ምን ማድረግ እንደሚችል ትኩረት አድርጎ እየሠራበት መሆኑንም ነው ርዕሰ መስተዳድር ሙስጠፌ መጠቆማቸውን ፋና ዘግቧል፡፡



## ከ1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ መሰራጨቱን የአማራ ክልል አስታወቀ

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- ከ1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ መሰራጨቱን የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ የሆኑት አቶ አጀበ ስንሻው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት በክልሉ እስከ አሁን አንድ ሚሊየን ሁለት መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሮች ተሰራጭቷል፡፡

በዘንድሮው ዓመት 8 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ ታቅዶ ሲሠራ እንደነበረ ጠቁመው በተፈጠረው ዓለማቀፋዊና አገራዊ ችግር የታቀደውን ያህል ማግኘት ባለመቻሉ በፌዴራል መንግሥት በኩል ለክልሉ የቀረበው የዕቅዱን 58 ፐርሰንት የሚሸፍን 4 ነጥብ 8 ሚሊየን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

2 ነጥብ 7 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ እስከአሁን ወደ ክልሉ ተጓጉዞ የደረሰ ሲሆን ይህም ግዢ ከተፈጸመበት 56 ፐርሰንት ያህሉ ነው፡፡ ከቀረበው የአፈር ማዳበሪያ 44 ፐርሰንቱ ለአርሶ አደሩ መድረስ መቻሉን ጠቁመው የተወሰነ መጠን የከረመ የአፈር ማዳበሪያ በመኖሩ እጥረቱን በመቅረፍ ረገድ መጠነኛ እገዛ ማድረጉን ጠቁመዋል፡፡

አቶ አጀበ እንደገለጹት፤ በአማራ ክልል በዘንድሮ ዓመት 4 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር በማረስ 143 ሚሊዮን ኩንታል የማምረት ዕቅድን ማሳካት የሚቻለው የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦቱ ሲሳካ ቢሆንም ያጋጠመውን ችግር በማለፍ የታቀደውን ያህል ምርት ለማግኘት በሚገባ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የአፈር ማዳበሪያ በታቀደው መጠን አለመገኘቱና ዋጋው በኩንታል ከ3000 ብር በላይ መጨመሩ በዘንድሮ ዓመት ከአፈር ማዳበሪያ ጋር ተያይዞ ያጋጠሙ ችግሮች መሆናቸውን የጠቆሙት ምክትል ቢሮ ኃላፊው ችግሩን ለመቅረፍ እጥረቱን በተፈጥሮ ማዳበሪያ እና በፈሳሽ ማዳበሪያ የመሸፈን ሥራ እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

የአፈር ማዳበሪያ በክልሉ ከ 4800 እስከ 5000 ብር በኩንታል እየተሸጠ ሲሆን አርሶ አደሩ የሚሸጣቸው ምርቶች ዋጋቸው በመጨመሩ ምክንያት በጥሬ ገንዘብ የመግዛት አቅሙ ስላደገ የአፈር ማዳበሪያ በጥሬ ገንዘብ ገዝቶ እንዲጠቀም እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

እስከአሁን በመንግሥት በኩል የሚደረግ ድጎማ እንደሌለ የገለጹት ምክትል ቢሮ ኃላፊው የመግዛት አቅም የሌላቸው አርሶ አደሮች የቅድሚያ ክፍያ በመክፈል በብድር ወስደው እንዲጠቀሙ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አርሶ አደሮች እንደ ማሳቸው ስፋት ከ2 እስከ 30 ኩንታል የተፈጥሮ ማዳበሪያ የሚጠቀሙ መኖራቸውን ተናግረው አርሶ አደሩ ከተፈጥሮ ማዳበሪያ በተጨማሪ በአንዳንድ ፋብሪካዎች የሚቀርበውን ፈሳሽ ማዳበሪያ በመጠነኛ ዋጋ ገዝተው መጠቀም እንደሚችሉም ጠቁመዋል፡፡

ምክትል ቢሮ ኃላፊው አክለውም ሳይታረስ የሚያድር ማሳ መኖር እንደሌለበት ጠቁመው በክልሉ ያለው የእርሻ መሬት ሙሉ በሙሉ በመንግሥትና በአርሶ አደሩ ጥረት መሸፈን ስላለበት አርሶ አደሩ ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሔ በማበጀት ማሳውን በሰብል መሸፈን እንዳለበት አሳስበዋል።

# ኦልማ በመጪው ክረምት በ51 ፓርኮች ውስጥ የችግኝ ተከላ ሊያካሂድ ነው

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- በክረምቱ ወቅት በ51 የአረንጓዴ ልማት ጥብቅ ፓርኮች ውስጥ ችግኞች ለመትከል ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የኦሮሚያ ልማት ማህበር /ኦልማ/ አስታወቀ።

የኦሮሚያ ልማት ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ደጀኔ ኢቲቻ እንደገለጹት፤ ኦልማ ከየአካባቢው አርሶአደሮች ጋር በመተባበር በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ 51 ፓርኮች ውስጥ ከአምስት ሚሊዮን በላይ ችግኞች ለመትከል የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እያከናወነ ይገኛል።

በመጪው ክረምት በጥብቅ የአረንጓዴ ልማት ፓርኮቹ ውስጥ የማንጎ፣ የአናናስና ሌሎች የፍራፍሬ ችግኞች እንዲሁም የተለያዩ ስነምህዳሩን ለመጠበቅ የሚረዱ አገር በቀል ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል። በዚህም የየአካባቢውን ኅብረተሰብ ያሳተፈ የችግኝ ጉድጓድ ቁፋሮና የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ዝግጅቶች በመከናወን ላይ ናቸው ብለዋል።



አቶ ደጀኔ ኢቲቻ

ለአብነት ከ51ዱ ፓርኮች ትልቁና አንዱ በሆነው በሰበታ ሃዋስ አካባቢ በሚገኘው የደበል ተራራ በመጪው ክረምት በስድስት ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ችግኝ ለመትከል የሚያስችል የዝግጅት ሥራ አርሶ አደሩን ባሳተፈ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኦልማ አካባቢውን ተረክቦ የአረንጓዴ ልማትና ጥበቃ ሥራ ማከናወን ከጀመረ ስምንት ዓመት እንደሆነው ተናግረው፤ እስካሁን 14 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የአካባቢ ጥበቃ ሥራ መከናወኑን አንስተዋል።

በተመሳሳይ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ጥብቅ ፓርኮች ውስጥ አርሶአደሮችንና የየአካባቢውን አስተዳደር ባሳተፈ መልኩ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚያስችሉ የአረንጓዴ ልማት ዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለችግኝ ዝግጅት ማድረግ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ቀደም ስለተተከሉት ችግኞች እንክብካቤና ስለቀጣዩ ሥራም የሚረዳ ውይይት በየአካባቢው እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

በ51ዱ ፓርኮች የሚከናወነው የችግኝ ተከላ ሥራው በርካታ አካላትን የሚያሳትፍና የሥራ ዕድልም የሚፈጥር ነው ያሉት አቶ ደጀኔ፤ ችግኞቹን በማፍላትና በማቅረብ ገቢ የሚያገኙ እንዳሉ ሁሉ የትራንስፖርት አማራጭ ከማቅረብ አንስቶ ተያያዥ ሥራዎችን ለሚያከናውኑ የሥራ ዕድል እንደሚፈጠርላቸው ገልጸዋል።

ከዚህ ባለፈ ውጤታማ የአካባቢ ጥበቃ ሥራ በተከናወነባቸው ስፍራዎች ላይ የአካባቢው ስነምህዳር በመመለሱ ንብ ማነብና ለእንስሳት እርባታ የሚሆን ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ተናግረዋል።

ለአብነት በደበል ተራራ ከዚህ ቀደም በተከናወኑ ሥራዎች አማካኝነት የንብ ቀፎዎች ተዘጋጅተው በዘላቂነት የማር ምርት ለመሰብሰብ የሚያስችል ዕድል መፈጠሩን አስታውቀዋል።

በኦሮሚያ ክልል ደበል ተራራ አካባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮችም ማኅበሩ የሚያቀርባቸውን የተለያዩ ድጋፎች መሠረት አድርገው በመጪው የክረምት ዘመን በርካታ ችግኞች ለመትከል የሚያስችል የጉድጓድ ቁፋሮ እያከናወኑ መሆኑን አርሶአደር አቶ ባልቻ ቱሉና ወይዘሮ ድንቂቱ ሻቃ ገልጸዋል።

በኦሮሚያ ከሚገኙና ጥብቅ የአረንጓዴ ልማት ስፍራዎች መካከል አንዱ የሆነውና በኦልማ የሚለማው የደበል ተራራ ከዛሬ ስምንት ዓመት በፊት ምንም ዛፍ የማይታይበት የተራቆተ ስፍራ መሆኑን አርሶአደሮቹ አስረድተው፤ ከአካባቢው ኅብረተሰብና አስተዳደር ጋር በመተባበር በተተከሉ ችግኞች አካባቢውን መልሶ በመልማት ላይ መሆኑን አስታውቀዋል።

በቀጣይም ማኅበሩ በሚያቀርበው ድጋፍ የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል የሚረዱና ለእርሻ ሥራ ምቹ የሆኑ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን በማጠናከር ጥብቅ ፓርኩን እንደሚያለሙ አርሶአደሮቹ ገልጸዋል።

ዜና

# ወደ ትግራይ ፥-

- ለሰብዓዊ ድጋፍ የሚውል ከ1 ነጥብ 87 ቢሊዮን ብር በላይ ተልኳል
- ከ400ሺ በላይ ሊትር ነዳጅ ተጓጉዟል
- ሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረስ 223 የአየር በረራ ተካሂዷል

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡ ለትግራይ ሕዝብ ሰብዓዊ ድጋፍ የሚውል ከ1 ነጥብ 87 ቢሊዮን ብር በላይ ወደ ትግራይ የተላከ መሆኑን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ ዘውዴ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት ለትግራይ ሕዝብ የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ መንግሥት ትኩረት በመስጠት ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሮ ድጋፉ እንዲደርስ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በክልሉ ለሚገኙ አምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ለሚደርሱ ሕዝቦች የገንዘብ፣ የመድኃኒት፣ የተመጣጠነ ምግብ እንዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች በማድረግ ዜጎች ለከፋ ጉዳት እንዳይዳረጉ በማድረግ ረገድ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አስታውቀዋል።

ሰብዓዊ ድጋፉ በርካታ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን ያካተተ መሆኑን ያስታወቁት አቶ ደበበ፣ 93 ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ ድጋፍ ተቋማት ምግብና መድኃኒትን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ድጋፎችን ለክልሉ ዜጎች በመስጠት ላይ እንደሚገኙ አንስተዋል።

በዚህም እስከ ግንቦት የመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ድረስ 1 ነጥብ 87 ቢሊየን ብር በጥሬ ገንዘብ ዝውውር በበርካታ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ድጋፍ ላይ በተሰለፉ አጋር አካላት ለሰብዓዊ ድጋፍ አቅርቦት በአየር ትራንስፖርት ወደ አካባቢው ማመላለሳቸውን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ደበበ ገለፃ 202 ሺህ 79 ኪሎግራም



አቶ ደበበ ዘውዴ

የመድኃኒት አቅርቦት በነዚህ የተለያዩ አጋር አካላት ቀርቧል። የተመጣጠነ ምግብ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ደግሞ ከ409 ሺህ 322 በላይ በኪሎግራም ሰብዓዊ አገልግሎት ለሚፈልጉ ወገኖች መደረጉን አንስተዋል።

ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን በተመለከተም በነዚህ ሰብዓዊ ድጋፍ በሚያቀርቡት ድጋፍ በኩል 11ሺህ 43 ሜትሪክ ቶን ወደ ትግራይ መላኩን አቶ ደበበ አንስተዋል።

402 ሺህ 229 ሊትር ነዳጅ ወደ መቀሌ ተጓጉዟል። በዚህ አገልግሎት አንድ ሺህ 947 ተሽከርካሪዎች የሰብዓዊ ድጋፉን ያጓጓዙ ሲሆን እስካሁን ድረስ ለሰብዓዊ አገልግሎት የተከናወነ በረራ ደግሞ 223 እንደሆነ አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል በሳዑዲ አረቢያ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ 102 ሺህ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያንን ወደ ሀገራቸው ለማስገባት በተሠራው ሥራ ካለፈው መጋቢት 21 ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ 75 በረራዎችን በማከናወን ከ28 ሺህ በላይ ዜጎች ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ ተደርጎዋል። በዚህም 25 በመቶ የሚሆኑ ዜጎች የተመለሱ ሲሆን ቀሪዎቹን ወደ ሀገራቸው የመመለስ ተግባር የሚቀጥል መሆኑን ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በኩል የአቀባበል፣ አሸኛኘት፣ የመኝታ፣ የምግብ አቅርቦት፣ የጤናና የስነ-ልቦና፣ ነፃ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሁም ትምህርት የሚሰጥበትን ሁኔታ ከባለድርሻ መሥሪያ ቤቶች ጋር በመሆን እየተሠራ እንደሚገኝ አመልክተዋል።

በዚህም ከ26ሺህ ስምንት መቶ በላይ ዜጎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር የተገናኙ ሲሆን ሌሎች መዳረሻቸው ትግራይ ክልል የሆኑ አንድ ሺህ 854 የሚደርሱ ዜጎች በአዲስ አበባ መጠለያ ጣቢያ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

## የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በቅድመ ዝግጅት ሥራው ጠቃሚ ግብዓቶችን እንዳገኘ አስታወቀ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እያከናወነ ባለው የቅድመ ዝግጅት ሥራ ለዋናው ውይይት ጠቃሚ ግብዓቶችን እንዳገኘ አስታወቀ።

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ዮናስ አደዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ከተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት ጋር ያደረጋቸውን ምክክሮችን ጨምሮ እያከናወናቸው ባሉ በርካታ ተግባራት ለዋናው የምክክር ሂደት ምዕራፍ ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ግብዓቶችን አግኝቷል። ዋናውን ዓላማ ለማሳካትም አስቻይ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ነው።

ኮሚሽነሩ፤ "ቅድመ ዝግጅቶች ለምናደርገው የዝግጅትና የሂደት መርሐ ግብሮች ጠቃሚ ናቸው። የሌሎች አገሮችን ልምድ እስካሁን ስናይ ነበር። አገራዊ ማንነትን ያንጸባረቀና በመጨረሻም ጥሩ ውጤት ያስገኙ ልምዶችን መውሰድ ተችሏል። ያልተሳካላቸውንም አገራት ልምድ ለማየት ተሞክሯል። ከሁለቱም ለኢትዮጵያ የሚበጅ የቱ ነው የሚል ልምድ ተወስዷል" ብለዋል።

እስካሁን የተከናወኑ ተግባራት አበረታችና ለቀጣይ ሥራ አጋዥ መሆናቸውን ያነሱት ኮሚሽነሩ፤ የሌሎች አገሮችን ልምድ መመልከታቸውን፤ ለአብነትም አገራዊ ምክክሩ ከተሳካላቸው እንደ ቱኒዚያና ኮሎምቢያ የመሳሰሉ አገራት ልምድ ማየት እንደተቻለና ጠቃሚ ግብዓት መገኘቱን ጠቅሰዋል።

በቱኒዚያ የተካሄደው ብሔራዊ ምክክር አጀንዳው ከወጭ የመጣ ሳይሆን በአገር አቀፍ ደረጃ በሕዝቡና በመንግሥቱ እንዲሁም በሲቪል ማኅበራት አማካኝነት ብቻ የሚመራ እንደነበር ኮሚሽነሩ አንስተዋል። ይህም አገራዊ ማንነትን ያንጸባረቀ በመጨረሻም ጥሩ ውጤት ያስገኘ ልምድ እንደነበር ጠቅሰዋል። ይህ አይነቱ ሂደት ለኢትዮጵያ ጠቃሚ ልምድ እንደሆነም ገልጸዋል።

አገር ውስጥ ያለው ዐውድ ለመረዳት ከሃይማኖት መሪዎች፣ ከአገር ሽማግሌዎች፣ ከአባገዳዎች ከሠላም እናቶችና ከሌሎችም ጋር መነጋገር እንደተቻለ በመግለጽ፤ ይህም የአገሪቷን ባህል በመረዳት ስለ ምክክርና ውይይት



ዶክተር ዮናስ አዳዬ

ጥሩ ግብዓት ያስገኘ ተግባር ነው ብለዋል። ኮሚሽኑ በቀጣይ ለሚያከናውናቸው ተግባራት ጉልበት መሆን የሚችሉ ተሞክሮዎች እንደሆኑም አመላክተዋል።

ከማኅበረሰቡ ጋር አብረው መሥራት ከሚችሉ አካላት ጋር መነጋገር የኮሚሽኑን ሥራ የበለጠ ለመገንዘብ እንዳስቻለም ኮሚሽነሩ ተናግረዋል። በተለይ "ከተፎካካሪ ፓርቲዎችና ገዢው ፓርቲ ጋር አንድ ላይ ለመሥራት መስማማታችን" ለዋናው የውይይት ምዕራፍ ጠቃሚ ግብዓት ነው ሲሉም ገልጸዋል። አንዳንድ የተቃወሙ ቢኖሩም በኋላ ላይ ግን ተወያይተው አብሮ ለመሥራት ቃል እንደገቡና ይህ አብሮነት ደግሞ ለአገሪቷ ጠቃሚ መፍትሔ ለማምጣት አስቻይ ሁኔታ ከመሆኑም በላይ ኮሚሽኑን የሚያበረታቱና የሞራል ስንቅ እንደሆኑ ነው የተናገሩት።

በቅድመ ዝግጅቱ ከብዙኃን መገናኛ ጋር የተደረገው ምክክርም አዎንታዊ ጉልበት ያለውና ዋናው አገራዊ ምክክር ስኬታማ እንዲሆን ለአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ጠቃሚ የሆነ ግብዓት እንደሆነ ጠቅሰዋል። እነዚህና መሰል ቅድመ ሥራዎች ከክልል ጀምሮ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ሥራዎችን በተቀናጀ መንገድ ለማስኬድ አጋዥ እንደሆኑ አስታውቀዋል።



## ለሲሚንቶ የምርትና የግብይት ሰንሰለት ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት እየተሠራ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በሲሚንቶ ምርት እና የግብይት ሰንሰለት ላይ የታዩ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት እየተሠራ መሆኑን የማዕድን ሚኒስቴር ገለፀ፡፡

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጅነር ታከለ ኡማ፤ በሲሚንቶ ምርትም ይሁን የግብይት ሰንሰለት ላይ ችግሮች መኖራቸው የተረጋጋ የሲሚንቶ ገበያ እንዳይኖር እና የዋጋ ንረት እንዲኖር ማድረጋቸውን ተናግረዋል፡፡

ለአብነትም ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ላይ የሚሸጠው አንድ ኩንታል በአማካይ 471 ብር መሆኑንና አዲስ አበባ ሲገባ እስከ 1 ሺህ ብር ድረስ እንደሚሸጥ አንስተዋል ይህንን ችግር ለመፍታትም ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የሲሚንቶ ዘርፍ ወደ ማዕድን ሚኒስቴር የገባው ከቅርብ ጊዜ ወደዚህ መሆኑን ያስታወሱት ኢንጅነር ታከለ፤ በፋብሪካዎች የሚታየው የምርት ችግር ምንጩ የተለያየ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ፋብሪካዎች በቂ ሲሚንቶ ምርት እንዳያመርቱ የውስጥ ማኔጅመንት ችግር፤ የአካባቢያዊ ሰላም እጦት እና የሠለጠነ የሰው ኃይል ችግር እንዳለባቸው ሚኒስትሩ አብራርተዋል

ተመሳሳይ ቴክኖሎጂ እና ተመሳሳይ ጥሬ እቃ የሚጠቀሙ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ተመሳሳይ የሰው ኃይል ብዛት ኖሯቸው የሚያመርቱትን ምርት ስናይ ትልቅ ልዩነት አለው ይህን ባደረግነው የዳሰሳ ጥናት ማረጋገጥ እንደቻልነው ዘርፉ ላይ ከማኔጅመንት ጀምሮ የሚታዩ ችግሮች እንዳሉ ነው ይህን መፍትሔ ለመስጠት ከፋብሪካዎቹ ጋር እየሠራን እንገኛለን ብለዋል፡፡

ሲሚንቶ ፋብሪካዎች በቀላልና ጥቃቅን የቴክኒክ ችግሮች ምክንያት ሥራ እንደሚያቋርጡ የገለፁት ኢንጂነር ታከለ፤ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች በሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ሥራዎቻቸው እንዳይስተጓጎሉ አብዛኞቹ ፋብሪካዎች በሚገኙበት በሆለታ አካባቢ በሚገኝ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ የሲሚንቶ ምርት ሥልጠና እንዲሰጥ እንቅስቃሴ መጀመሩን አብራርተዋል፡፡

በሲሚንቶ ዋጋ ላይ ተፅዕኖ ያለው አንዱ በየአካባቢው የሚፈጠረው የሰላም እጦት ነው ይህን ከክልሎች ጋር በመነጋገር እና የመከላከያ ሠራዊቶች በፋብሪካዎች እንዲሠማሩ በማድረግ አንፃራዊ ሰላም እንዲሰፍን መደረጉን ተናግረዋል፡፡

የፀጥታ ኃይል በማሠማራት ብቻ ችግሮች በዘላቂነት ስለማይፈቱ ለፋብሪካዎች ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን ወጣቶች እንዲያመርቱ በማድረግ ችግሮች እየተፈቱ መሆኑን ሚኒስትሩ ገልፀዋል

የሲሚንቶ ዋጋ ንረትን ለማስቀረት መንግሥት በዘርፉ ውስጥ የተሰገሰጉ ዕሴት የማይጨምሩ አካላት እንዲወጡ ማድረጉን እና ግብይቱ በአጠረ የግብይት ሰንሰለት እንዲካሄድ ለማድረግ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ገልጸዋል፡፡

ክልሎች ለሲሚንቶ ምርት የሚሆን ቦታ አዘጋጅተው ፋብሪካዎች ምርታቸውን በክልሎች ወደተዘጋጀ መጋዘን እንዲያስገቡና የክልል መንግሥታት ይህንን እንዲቆጣጠሩ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል በዚህም ከማምረቻው ጀምሮ በክልሎች እና በአዲስ አበባ ያለው የሲሚንቶ ዋጋ ፍትሐዊ ይሆናል የሚል እምነት እንዳላቸው ሚኒስትሩ ገልፀዋል፡፡

ዜና

# መንግሥት ለነዳጅ የሚሆነውን ወጪ ለመሸፈን የሚያስችለውን አማራጭ ማስፋት እንዳለበት ተገለጸ

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት ለነዳጅ የሚሆነውን ወጪ ለመሸፈን የሚያስችለውን አማራጭ ማስፋት እንዳለበት በዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ዶክተር ደም መላሽ ሀብቴ ገለጹ። የአሁኑን አይነት ዓለማቀፍ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪዎች እንደኢትዮጵያ ያሉ ሀገራትን አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያስገባል ሲሉም አመላክተዋል።

ዶክተር ደምመላሽ ዓለማቀፍ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪን በሚመለከት ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፤የኢትዮጵያ መንግሥት ለነዳጅ ድጎማ የሚሆነውን ወጪ ለመሸፈን የሚስችለውን ገንዘብ ለማሟላት አማራጮችን ማስፋት አለበት ሲሉ ተናግረዋል።

መንግሥት በየዓመቱ የነዳጅን ዋጋ ለመደጎም በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ከካዝናው እንደሚያወጣ የገለጹት ዶክተር ደመላሽ፤ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የታክስ ባህል ባልዳበረበት ሀገር ውስጥ ለነዳጅ ክፍያ ብቻ የሚውል ገንዘብ ማግኛ መንገዶችን ማብዛት ለነገ የማይባል ሥራ መሆኑን አመላክተው በብድርም ይሁን በስጦታ የሚገኙ ገቢዎችን ወደ ዘርፉ ማዋል እንደሚገባም ገልጸዋል።

የአሁኑን ዓይነት ዓለማቀፍ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪዎች እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በኢኮኖሚው ዘርፍ ያላደጉ ሀገራት መንግሥታትን አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያስገባሉ ሲሉ የገለፁት ዶክተር ደም መላሽ፤ ወጪውን ለመሸፈን መንግሥትም ሆነ ግለሰቦች በተባበረ መንገድ መፍትሔ ሊፈልጉለት የሚሻ ጉዳይ መሆኑን አመላክተዋል።

መንግሥት ገቢ ከማስፋት በተጓዳኝ የተለያዩ ምሑራንን፣ የተፎካካሪ ፖለቲካ አመራሮችን እንዲሁም የሚመለከታቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች በማማከር ለጉዳዩ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ መፍትሔዎችን ሊያፈላልግ እንደሚገባው ገልፀዋል።

ዶክተር ደም መላሽ በገለፃቸው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰበሰበው የታክስ መጠን በጣም አነስተኛ መሆኑን የገለፁ ሲሆን፤ በአብዛኛው ለሀገራቸው በታማኝነት ታክስ የሚከፍሉት የመንግሥት ሠራተኞች መሆናቸውን ገልጸው፤ ከፋብሪካና ከትልልቅ ዘርፎች የሚሰበሰበው የታክስ መጠን እጅግ አነስተኛ መሆኑንም አብራርተዋል።

መንግሥት ከግብርናው ዘርፍ ጭምር ታክስ በመሰብሰብ የነዳጅ ወጪውን መደጎም እንዳለበትም ዶክተር ደም መላሽ ገልጸዋል።

የኢኮኖሚ ባለሙያው እንዳሉት በአፍሪካ ከሚገኙት ሀገራት መካከል ነዳጅ በርካሽ ከሚሸጥባቸው ሶስት ሀገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ናት። ከጎረቤት ሀገሮች አንጻር በኢትዮጵያ ውስጥ በዓለምአቀፍ ደረጃ ከሚሸጥበት የነዳጅ ዋጋ አንፃር ከግማሽ በታች ነው እየተሸጠ እንደሚገኝ ጥናቶች ያመለክታሉ።



ዶክተር ደም መላሽ ሀብቴ

## በመኸር ግብርና 390...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሚሊዮኑ አርሶ አደሩ እጅ መግባቱን አሳውቀዋል።

በማዳበሪያ ፍላጎት መጨመር ለሚከሰተው የማዳበሪያ እጥረት ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ /ኮምፖስት/ በማዘጋጀት ክፍተቱን ለማሟላት አቅጣጫ ተቀምጧል።ከአቅርቦትና ስርጭት ጋር ለሚነሱ ጥያቄዎችን ለመፍታት ባለሙያዎች ተመድበው መፍትሔ የሚገኝበት መንገድ በማስቀመጥ ችግሮችን ለመቀነስ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ዘንድሮ የአየር ሁኔታው ጥሩ በመሆኑ በመኸር ግብርና 390 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት መታቀዱን ገልጸው፤ ይህንን ስኬታማ ለማድረግ ባለሙያና በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና ወጣቶች ድጋፍ ማድረግ አለባቸው ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በሌላ በኩል በአራት ዓመት ውስጥ ለማከናወን ዕቅድ የተያዘለትን የአረንጓዴ አሻራ ለማጠናቀቅ ከስድስት ቢሊዮን በላይ ችግኝ ተዘጋጅቷል። ከዚህ ውስጥ 50 በመቶዎቹ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የፍራፍሬና ችግኞች ናቸው ብለዋል።

ለመጪው ክረምት ችግኝ ተከላ የመሬት ዝግጅት መጀመሩን ገልጸው፤ የተከላው ሙሉ መርሐ ግብር በሰኔ ወር በይፋ እንደሚጀመር ጠቁመዋል።

ድርቅና የጸጥታ ችግር ባለበት ቦታዎች የሚኖሩ ዜጎች በምግብ እራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ በአንድ ቢሊዮን ብር ዘር ተገዝቶ መቅረቡን አያይዘው ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን የሚተኩ ምርቶችን በማዘጋጀት፣ በበጋ መስኖና መሰል የግብርና ሥራዎች እንዲስፋፉ የሚረዱ 10 ፕሮግራሞች ተዘጋጅተዋል ብለዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ ድርቅና የጸጥታ ችግሮችን በመቋቋም 900 ሚሊዮን 336 ኩንታል የእህል ምርት ማዘጋጀት ተችሏል።በበጋ መስኖ ሰንዴ ምርትን ተግባራዊ በመደረጉ ምርታማነትን ከመጨመሩንም በላይ የሚታረሰው የመሬት ስፋትም በዓመት በእጥፍ ጨምሯል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአስቀመጡት አቅጣጫ መሠረት የከተማ ግብርናና የጓሮ ግብርና ለማጠናከር በከተማና በከተሞች ድንበር አካባቢ በሚካሄዱ የግብርና ሥራዎች ግንዛቤ ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ባለፈ መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ በሰጠው ትኩረት አንድ ምርት ከተመረተበት ቦታ አንስቶ እስከሚሸጥበት ስፍራ እስኪደርስ በቴክኖሎጂ መከታተል የሚያስችል አሠራር እየዘረጋ ነው ብለዋል።

ከለውጡ በፊት የነበረው አሠራር አንድ ምርት ከተመረተበት ቦታ ወደ ውጪ ሀገር ሲላክ በመሐል ብዙ ችግሮች ሲያጋጥሙ እንደነበር አስታውሰው፤ በጉዳዩ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ቡናን ጨምሮ በባቡር ብቻ እንዲጓጓዝ ተወስኗል። ይህም ግብይቱን ግልጽነት እንዲኖረው በማድረግ አምራቹን ተጠቃሚ እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

## “በኦሮሚያ ክልል ውስጥ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሕጻናትን ጨምሮ እድሜያቸው 80 ዓመት የሆናቸውን አዛውንቶችን የደፈረ፤ ሰዎችን በማፈን ገንዘብ የሚጠይቅ፤ እናትን ከነልጇ እንዲሁም ልጅን እናት ፊት የገደለ፤ ቤተሰብን በአንድ ቤት ውስጥ በእሳት ያቃጠለ አጥፊ ቡድን ነው።

ከዚህ ቀደም ቡድኑ ላይ እርምጃ ሲወሰድ የነበረ ቢሆንም፤ የጁንታው ቡድን ወረራ በፈጸመ ጊዜ ሁሉም አቅሙን አገርን ከጥቃት የመከላከል ሥራ ላይ ትኩረት አድርጎ ሲሠራ ሸኔ ማንሰራራቱን፤ በአገር ሽማግሌ ጭምር ወደ ሠላማዊ የትግል እንቅስቃሴ እንዲመለስ ቢጠየቅም አሻፈረኝ በማለት አንዱ አዲስ አበባ በመሆን ሌላው ጫካ በመሆን የእኩይ ተግባሩን መቀጠሉን፤ በዚህ ምክንያት መንግሥት ባደረገው ሰላም የማስጠበቅና ሕግ የማስከበር ኦፕሬሽን በቡድኑ ላይ እርምጃ መውሰዱንና በዚህም ለበርካታ ጊዜ እጅ የሰጡና የመደምሰስ እርምጃ የተወሰደባቸው የሸብር ቡድኑ አባላት መኖራቸውን ጠቁመዋል።

ተታለው ወደ ሽብር ቡድኑ የተቀላቀሉ በተለያየ ጊዜ እጃቸውን ለመንግሥት በመስጠት ከጥፋታቸው መታረም እንደቻሉም አስታውቀዋል።

በክልሉ በአሁን ወቅት የሸኔ ቡድን የተቆጣጠረው አንድም ቦታ እንደሌለ በመጥቀስ፤ ቡድኑን በማጥፋት ረገድ የሕዝቡ ተሳትፎ ከፍተኛ እንደነበርና በአሁን ወቅት በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች አንጻራዊ ሰላም እንዳለ አመልክተዋል። ሕዝቡም ሰላማዊ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል ብለዋል። ኦፐሬሽኑ ንጹሐንን በማይጎዳ መልኩ መካሄዱንም ተናግረዋል። የሽብር ቡድኑን እስከ መጨረሻው ለማጥፋት ሁሉም ባለ ድርሻ አካል ትብብር ሊያደርግ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

## የሀገርን ዳር ድንበር ለመጠበቅ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከወታደሮች ብዙ የተግባር ልምድ የሚያገኙ በመሆኑ በየቀኑ ማንበብን፣ መማርን፣ አካባቢን ማጥናትንና አካባቢን መመርመርን አብዝተው የሚወዱ መሆን አለባቸው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ጀግና ካለ እውቀት ሙሉ አይሆንም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ጀግንነት፣ ዓላማንና እውቀትን ሳትነጣጥሉ በማጣመር በየዕለቱ በማዳበር የኢትዮጵያ ኩራት የምትሆኑ መኮንኖች መሆን ይጠበቅባችኋል።ኢትዮጵያውያን አሸናፊዎች ነበርን፤ አሸናፊዎች ሁነን እንቀጥላለን፤ ኢትዮጵያዊነትን ማሸነፍ አልተቻለም፤ ወደፊትም አይቻልም።ይህ የሚረጋገጠው የአሸናፊነት ስነልቦናን የተላበሰ ወታደራዊ ተቋምና መኮንኖች ሲኖሩን በመሆኑ ተመራቂዎች ለሀገር አንድነት መሥራት ይኖርባችኋል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

የተመረቃችሁበት አካዳሚ ብዙ ጀግኖችን ያወጣ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር፤ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ለመሆን የወሰናችሁበት ዛሬ ምክትል መቶ አለቃ የምትባሉ ነገር ግን በውስጣችሁ ብዙ ጄኔራሎች፣ ብዙ የሀገር መሪዎች፣ የሀገር ኩራቶች የሚፈጠሩበት ታሪካዊ እለት ነው ብለዋል።በሚቀጥለው የሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ የማይረሳ ታሪካዊ ቀን ስለሆነ የዛሬ ምክትል መቶ አለቃዎች የነገ ጀነራሎች እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በበኩላቸው፤ ከለውጡ በኋላ የጦር ሠራዊታችን የግንባታ ስትራቴጂ አቅጣጫ መሠረት የኢትዮጵያ ወታደራዊ አካዳሚ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ ቁጥር ያለው እጩ መኮንኖችን ተቀብሎ በጥራት በማሰልጠን ባለፉት ዓመታት ተፈጥሮ የነበረውን የዕጩ መኮንኖች ስልጠና ክፍተት የሞላ ነው ብለዋል፡፡

የዘንድሮ ተመራቂዎች ልዩ የሚያደርጋቸው ብዙዎች በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው መሆኑ ነው ያሉት ፊልድ ማርሻሉ፤ ተመራቂዎች ሀገራችን ችግር ውስጥ በገባችበት ጊዜ የከፍተኛ ትምህርታችሁን በመተውና ሥራችሁን በመልቀቅ ሀገራችሁን በውትድርና ሙያ ለማገልገል በራሳችሁ ፍቃድ ወስናችሁ ስልጠናውን በማጠናቀቃችሁ የሀገር ተስፋ ናችሁ ብለዋል።በቀጣይም እንደ አንድ ጀማሪ መኮንን የሚሰጣችሁን ግዳጅ በብቃት እንደምትወጡ እተማመናለሁ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ምርቃቱ የሚያሳየው ሠራዊታችን ዛሬም እንደ ትናንቱ የጀግኖች መፍለቂያና በጠንካራ መሠረት ላይ እየተገነባ መሆኑን ነው ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፤ ከምረቃው በኋላ በምትሠማሩበት ክፍል የምትቀላቀሉት ሠራዊታችን እንደ ወርቅ በእሳት የተፈተነ፤ ከራስ በፊት ሕዝብና ሀገርን ያስቀደመ፤ በወታደራዊ ሥነሥርዓት የታነጸ፣ ለማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የማይወግን ነው።በመሆኑም በስልጠና ወቅት የቀሰማችሁትን እውቀት ወደ ተግበር ለመቀየር በፍጥነት ከሠራዊቱ ጋር በመዋሃድ ውጤታማ መሪ ለመሆን ዝግጁ መሆን ይጠበቅባችኋል ሲሉ አሳስበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢትዮጵያን ጥሪ እናድምጥ፤ ለጥሪዋም መልስ እንስጥ!

ሀገር የማንነት ብቻ ሳይሆን የሕልውና ማጽኛ ሥር ናት። ሥር ደግሞ በባህሪው ወደ ውስጥ ጠልቆ በመግባት የላዩን አካል የሚመግብ፤ ሚዛኑን ጠብቆ እንዲዘልቅም ተሸክሞ የሚያኖር ታላቅ መሠረት ነው። የዛፉ ሕልውና የሚወሰነውም ከሥሩ መኖር አለመኖር ጋር በመሆኑ፣ ሥር ለዛፉ ሕልውና የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን አማራጭ የሌለው በምንም የማይተካ ነው። ሀገርም ዜጎቿ እንዲሁ ናት፤ ዜጎች ማንነታቸውን የሚገልጹትም፤ በማንነታቸው ከፍ ብለው የሚታዩትም፤ የመኖራቸውን መሠረት የሚያጸኑትም፤... በሀገር ላይ ነው። ሀገር ካለች ይኖራሉ፤ አገር ከሌለች ማንነታቸውም፤ መሠረታቸውም ተናግቶ ይበተናሉ።

ለዚህም ነው ሀገር በሰው፤ ሰውም በሀገር ጸንተውም ደምቀውም መኖራቸው። ሀገር ያለ ሰው ባዶ አና ናት፤ ሰውም ያለ ሀገር ማንነት አልባ ነው። ባዶነትም፣ ማንነትም እንዳይጠፉ የሀገር እና የዜጎቿ ቁርኝትና መጠባበቅ የግድ ነው። ዛፍ ያለ ሥር ሕልውና እንደሌለው ሁሉ፤ ሀገርም ያለ ሰው፣ ሰውም ያለ ሀገር ምንም ናቸው። ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ደግሞ ይሄ ከምንም ቀድመው የተረዱ፤ በፍጹም ልብ በፍቅር ተጋምደው የኖሩና የሚኖሩ፤ አንዳቸው የአንዳቸው ማረፊያና መከበሪያ ሆነው በታሪክ ደምቀው የተጻፉ ሀገርና ሕዝቦች ናቸው።

ይህ የማይላላ የሕልውና ማስጠበቂያ ቁርኝት ትናንት ሀገርን ከመፍረስ ታድጓል፤ ሉዓላዊነትን ሳያስደፍር አዝልቋል፤ ሕዝቦች በማንነታቸው የማይሸማቀቁበትን፣ በኢትዮጵያዊነታቸው ደረታቸውን ነፍተው የሚናገሩበትን ልዕልና ገንብቷል። ይህ ግን የአባት አያቶቻችን ታሪክ ነው። ይህ የትናንትን ቀደምቶቻችን የሀገርና ባለ ሀገርነት ገድል ውጤት ነው።ይህ እኛ ከፊተኞቻችን ልንማርበት የሚገባን እውነተኛ የሀገር ባለቤትነት መንፈስ፤ ለዜግነት ከፍታ ሊከፈል የሚገባው ዋጋ ውጤት ነው።

ዛሬ ያለንበት ሀገራዊ ዐውድ ደግሞ ይሄንን የቀደምቶቻችንን ከፍ ያለ የሀገር ባለቤትነት ውርስ፤ ለሀገር ክብር የተከፈለውን የላቀ ዋጋ ተገንዝበን ልንጠቀምበት ግድ የሚለን ነው። ምክንያቱም ወቅቱ የውጪ ታሪካዊ ጠላቶች፤ የውስጥ ተላላኪ ባንዳዎችና አሸባሪዎች ኢትዮጵያን በእጅጉ እየፈተኗት፣ ሕዝቦቿንም ሊከፋፍሉ እየሠሩ በመሆኑ ነው። ሀገር የማፍረስ ውጥናቸውን ከዳር ለማድረስ ደግሞ፣ መጀመሪያ የሚሠሩት ጋሻ የሆነው ሕዝቧና አጥር የሆነው መከላከያ ሠራዊቷ ላይ ነው። ሕዝቧን በመከፋፈል የአንድነት ኃይሉን መናድ፤ መከላከያዋን ደጀን በማሳጣት ብቻውን ማቆምና ማጥቃት የእቅዳቸው ማጠንጠኛ ነው።

ይህ ሲሆን ሀገር ጠባቂና ተቆርቋሪ ታጣለች የሚለው ሕልማቸው መዳረሻው፣ የዘመናት ታላቅነቷ ላሰጋቸው የውጭ ጠላቶች መፈንጫ የምትሆን የተዳከመች ኢትዮጵያን መፍጠር ነው። ይህ እንዳይሆን ደግሞ የአባቶቻቸው ልጆች የሆኑት የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን የሚችሉትን ሁሉ ዋጋ እየከፈሉ መሆናቸው እሙን ነው። ይሁን እንጂ እዚህም እዚያም የሚረጨው ከፋ የአሉባልታና የፈጠራ ወሬ መርዝ እየተበራከተ፤ የኢትዮጵያዊነት ልካቸው መሠረቱ ያልጸና ኃይሎችን ጆሮ እየሳበ መሄዱ እየተስተዋለ ነው።

በሌላ በኩል አሸባሪው ሕወሓት እና ግብራበሮቹ የጦርነት ጉሰማቸውን ጀምረዋል። ይህ ደግሞ ሀገርን እንደ ሀገር ሕዝብንም እንደ ሕዝብ ወዳልፈለጉት ጦርነት ዳግም የሚያስገባ የከፋዎች እሳቤና ሕልም ውጤት ነው። ይህ እንዳይሆን ደግሞ በመንግሥት በኩል ለሰላም ያለውን ብርቱ ፍላጎት በተግባር እየገለጸ ይገኛል። ሆኖም ሕልውናውን በጦርነት ውስጥ ካልሆነ ማስቀጠል የማይችለው አሸባሪው ኃይል ይሄን የሰላም እጅ እየገፋ ዘልቋል፤ አሁንም ለሰላም የተዘረጋው እጅ እንዲታጠፍ የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ገብቷል።

የእነዚህ ሁነቶች ድምር ውጤት ደግሞ አገር ስለ ደህንነቷ፤ ስለ ልጆቿ ክብርና ሕልውና፤ ስለ ዜጎቿ ደህንነትና ሰላም ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ድምጿን እንድታሰማ አድርጓታል። በአንድ በኩል የሐሰት ትርክትና አሉባልታ በሕዝቧ ውስጥ ውዥንብር የሚፈጥር፣ የሚከፋፋልና አንድነቱን የሚያላላ እንደመሆኑ ይሄን ክፉ ነፋስ የሚገታ ትውልድና ዜጋ ትሻለች። በሌላ በኩል፣ አያሌ ልጆቿ በጦርነትም በድርቅም ተጎድተው እጆቻቸውን ለሰብዓዊ ድጋፍ ዘርግተው እየተማጸኑ እንደመሆናቸው እነዚህን ልጆቿን ሳይሰለች የሚመግብላት፣ በዘላቂነትም የሚያቋቁምላት ወገን አብዝታ ናፍቃለች። ከዚህ ጎን ለጎን ስለ ሕልውናዋ የተጋረጠባትን አደጋ፤ የሕዝቦቿን ሰላም ለመንጠቅ የጦር ነጋሪት ስለሚጎስምባት ጠላት፤ ስለ ሉዓላዊነቷ ከውስጥ ባንዳዎች፣ ከውጪ ታሪካዊ ጠላቶቿ ተቀናጅተው ስለሚሰነዝሩባት በትር፤... የሚመክትላት የቁርጥ ቀን ልጅ በየፈርጁ ትፈልጋለች።

ይህ ወቅት የዲፕሎማሲ ጀግና፤ የከፋፋይ ፕሮፖጋንዳን የሚያመክን ጀግና፤ ለወገኑ አለሁ የሚል ጀግና፤ ለሀገሬ ዳርድንበር መከበር፣ ለወገኔ ሰላም መስፈን በግንባርም በደጀንም አለሁ የሚል ጀግና፤ ወገኑን አምርቶ የሚመግብ አርብቶና አርሶ አደር ጀግና፤ ሕዝቡን በመልካም አስተዳደር የማያማርር፣ ከሌቦችና አሸባሪዎች ጋር የማይመሳጠር ጀግና አመራር፤... በሁሉም የሙያ መስክ፣ በሁሉም ደረጃና ቦታ ስለ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ሊተጋ፣ ዋጋም ሊከፍል የተዘጋጀ የቁርጥ ቀን ልጅ አጥብቃ የምትፈልግበት ነው።

ሁሉ ነገሩን ሊሰጥ በየዐውዱ በግንባር ተሰልፎ ያለው የመከላከያ ሠራዊት እንደ ምንጊዜውም በጊዜው ምላሹን የሰጠና የተሰጠ ሆኗል። ሆኖም በዲፕሎማሲውና በፕሮፖጋንዳው እንዲሁም በኢኮኖሚው መስክ ያለውን የጠላት ክንድ በወጉ ተገንዝቦ በልኩ የሚመክትላትን በምትፈልገው ልክ ያገኘች አይመስልም። እናም አገር የምትጠበቀው፤ ሕዝብ በአንድነቱ ጸንቶ የሚኖረው በመከላከያው ብቻ ባለመሆኑ፣ ሁሉም በየተሠማራበት እንዲሠራላት፣ ጥሪዋን ተቀብሎም እንዲሰማራላት ትሻለች። ጥሪዋን አድምጦ ምላሽ መስጠትም ከሁሉም ይጠበቃል።


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ለፍቅሩም፣ ለጠቡም፣ መጀመሪያ ሀገር ትኑር...!

ብስለት

አእምሯችን ነቅቶ ነገሮችን በጥልቀት እንዳን መለከት እንዳናስተውል የሆነ የተያዘብን ነገር ያለ ይመስለናል። ጠበብ ብለን ከአነሱት በታች ሆነናል። ዘር ጎጥ ቀበሌ መንደር እያለን በጥቃቅን ክፍልፋዮች ውስጥ የተቀበርን ስንቶቻችን ነን?። እኔ ዘረኛ አይደለሁም የምንልስ ከኔ ሀይማኖት የሚበልጥ የለም በሚል መታበይ የሌላውን የምንንቅ የምናንቋሽሽ ቤቱ ይቁጠረን። ግን ግን እውነት እንዲህ ተከታትፈን የአንድነት ስማችን ኢትዮጵያ የማትኖር ከሆነ የትኛው የተደበቅንበት ጉሬ ከመጥፋት ያስጥለናል?

ዛሬ ላነሳ የወደድኩት ሀሳብ ለመጠላቱም ለመታረቁም መጀመሪያ ሀገር ሊኖረን ይገባል የሚል ነው። ይህ ማለት አንድ ጠጣ መላ ሰውነቷ ላይ እሾህ ተሰክቶባት እሾኩን ሊለቅሙላት ለመጡት ባልንጀሮቿ መጀመሪያ መቀመጫዬን እንዳለችው ማለት ነው። ለመጣላትም ለመታረቅም፤ ለመደሰትም ለማዘንም፤ ለመሞትም ለመቀበርም መጀመሪያ መቀመጫ ያስፈልገናል። መቀመጫችንን ለማጥፋት የምንሯሯጥ ከሆነ ቁርጣችሁን እወቁ ኢትዮጵያ ሳትድን ማንም አይድንም።

ሀገራችን ፈርሳ፤ ሀገር ጠፍታ ብሄርህ አይድንም፤ ሀገር ሳትኖር ሀይማኖትህ አይድንም፤ እንደ ሰው መቆጠር ቀርቶ ሰው ሆኖ መቆምም ችግር ይሆናል። ስለዚህ ብሄሬን ብቻ አድናለሁ ብለን ከፍ ዝቅ የምንል፤ ሀይማኖቴን መሸሸጊያ አደርጋለሁ ብለን ደፋ ቀና ያለን የምንሰራው ስራ "ልፋ ያለው አንድ እንጨት ያስራል" እንደሚባለው አይነት ስራ መሆኑን አውቀን እንንቃ።

ኢትዮጵያ ሳትድን ኦርቶዶክስ የምትድን የሚመስለንም እንዲሁ ድከሙ ብሎን ነው እንጂ ኦርቶዶክስ ያለ ሀገር ከቶም አትኖርም። ጭራሽ ከሀገር ውጪ ኦርቶዶክስ አትታሰብም። ፕሮቴስታንት ነኝ፤ ካቶሊክ ነኝ እያልን ያደፈጥንም ሁሉ ጠንቅቀን ማወቅ የሚገባን ኢትዮጵያን ሊያጠፋ የመጣ አንተን ልጇን ለይቶ ሊተውህ የሚችልበት ምክንያት እንደማይኖር ነው። ኢትዮጵያ ሳትድን ከቶም የሀይማኖት ነጻነት ቀርቶ እንደ ሰው ቆሞ መኖር የሚታሰብ አይሆንም።

እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ሙስሊሞችም ልብ ብላችሁ አስተውሉ። ሀይማኖታችን መደበቂያ ማምለጫ የሚሆነን ጊዜ የሚኖረው መጀመሪያ መቀመጫችንን ለማዳን አንድ ሆነን ስንቆም ነው። ያለበለዚያ አብሮነታችን ውበታችን፤ የመከባበር የሀይማኖት እኩልነት ሀገር ያልናት እኛ ከውስጥ ከተፈረካከስንላቸው እንደ ተራበ አንበሳ ሊውጡን አሰፍስፈው ዙሪያችንን እየዞሩ ያሉ ሀይሎችን ኑ ዋጡን ብሎ እንደመጋበዝ ይቆጠርብናል።

እናም ሀገራችሁ ኢትዮጵያ ዛሬ በመላው አለም ቢሊዮኖች የሚያመልኩትን የእስልምና እምነት በፍትህ እና በእውነት ከመጥፋት የታደጋቸው፤ በዚያን ዘመን የነበሩ ክርስቲያን ነገስታት በሀይማኖት እኩልነት እና ነጻነት የሚያምኑ ስለነበሩ ነው:: እስልምናም ለሽህ ዘመናት በነጻነት በኢትዮጵያ በነጻነት ሲሰበክባትና ሲስፋፋባት የኖረባት ሀገር ስላላችሁ ነው። ዛሬ በመላው አለም ያሉ እውነተኛ ሙስሊሞች ወንድሞች በኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ታሪክ እንዴት እንደሚኮሩም ልብ ማለት ያስፈልጋል።

እናም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ነኝ የምንል ሁሉ አንድ ብቻ አላማ ይኑረን። በጋራ የምንቆምላትን የሁላችን ማረፊያ መቀመጫ የሆነችውን ኢትዮጵያን እናድን። አንድ ሆነን በተባበረ ክንዳችን ኢትዮጵያን እጃችን ውስጥ ካስገባን በኋላ በሜዳችን ችግራችንን እንፍታ። ኢትዮጵያን በመልመጥመጥ አድናለሁ ብለን እያሰብን ከሆነ ተሸውደናል:: ቆፍጠን ብለን ህዝብና ህዝብ አንድ የሚሆነበት መደላድል መፍጠር ነው የሚያሻን። እውነተኛ ኢትዮጵያዊ የሆናችሁ ሁሉ ኢትዮጵያን ለማዳን በጋራ ቁሙ። አንድ ራዕይ አንድ አቋም ብቻ ይኑረን። እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ከሆንን አንድ ሀገር ብቻ ናትና ያለችን እሷን ለማዳን የተቆራረጡ ክፍልፋይ አስተሳሰቦቻችንን ወዲያ ጥለን በአንድ እንጋመድ።

ጊዜ አምጥቶ በኢትዮጵያ ህዝብ መካከል የበተነው የጎሳ ፖለቲካ ለኢትዮጵያ ሰዎች ሁሉ መርገምት ሆኖበታል፤ ለጊዜው ይሄኛው ወይም ያኛው ጎሳ ያሸነፈ ይመስላል እንጂ በኢትዮጵያውያን መካከል ዘላለማዊ ፍጅት የሚያኖር የማይበርድ ቁርሾ ይዞ የሚያስቀጥል ነው። ታዲያ ያለፈ ታሪካችንን ለፍጅት መነሻ ሊሆነን አይገባም፤ ይልቁንም ካለፈው ተምረን የተሻለ አዲስ ታሪክ ልንጽፍ የተገባ ነው:: ይህ እንዲሆን ደግሞ እስኪ ክፍፍሉን አሸንፈን በአንድ እንቁም፤ በቅድሚያም እምዬ ኢትዮጵያችን ትዳን።

የጎሳ ፖለቲካ ፓርቲዎች አብሮ መኖር ካልተቻለ ጎሳዎችን መገነጣጠል ይሻላል እንደሚሉት፤ አለዚያም ምዕራባውያን መንግስታት የራሳቸውን ፍላጎት ብቻ ለማንበር ኢትዮጵያን ሰፋ ብላ ካስቸገረች በእነሱ ፍላጎት መሰረት መገነጣጠል እና አነስ አነስ ያሉ ታዛዥ ሀገራትን መፍጠር የሚለው ስሌትም እንዳይሰራ ለማድረግ እውነት የሀይማኖቶች ደሴት የአማኞች ሀገር የሆነችን ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሄር ከአፍ በዘለለ የእውነት ውስጣችን የተተከለውን የጎጠኝነት ሰንኮፍ ነቅለን እናድናት። አባቶቻችን እንደሚሉትም ኢትዮጵያ ቅድስት ኢትዮጵያ ነች።

እናም ምርጫችን ኢትዮጵያዊ የሆንን ቅድስናችንን ተቀብለን፤ የጎሳ ፖለቲካን ስሩን ነቅለን፤ ኢትዮጵያዊነት ማንነታችን ሰገነት ማማ ላይ ማንበር ብቻ በቂ ነው። የተፈጠርነው ተባልቶ ለማለቅ አለመሆኑን ተገንዝበን ፈጣሪ አለም ላይ ሲያመጣን ለተፈጠርንበት ሀሳብ የተመቸን ፈጣሪ ሰውን በመፍጠሩ እንዳይፀፀት የምናደርግ የቅድስት ሀገር ልጆች ቅዱሳን እንሁን። ሌላ ምርጫ የለንም ይህ ካልሆነ ግን እየተቀጣቀጥን አብረን በክፋት እና በጎሰኝነት እየተባላን ከሰውም ከአለምም በታች ሆነህ እየተገዳደልን እየተፋጀን እንኖራለን።

አለበለዚያ ቅድስናችንን አምነን ቅድስት ኢትዮጵያን ጠቅልለን እናድናለን። ያኔ የሁላችን የሆነች አንድ ሀገር ይኖረናል ማለት ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን በአንዲት የጋራ ሀገራችን አምነን እንዲሁም የኔ ብሄር ምረጥ የኔ ብቻ አንደኛ የሚለውን አመለካከት ወደጎን ትተን፤ የጎሳ ፖለቲካን ስሩን ቀጥቅጠን አድርቀን ወይም ከስሩ መንግለን በማቃጠል ኢትዮጵያውያን የቀደሙ ነገስታት አባቶቻችን እንዳስተማሩን አንዲት ሀገር ብለን መነሳት ካልቻልን የእውነት ከልቤ ነው የምነግራችሁ በዚህ በመከፋፈል አስተሳሰባችን ሀገራችን ጠፍታ ከቶም ማናችንም አንድንም።

የትኛውም ነገድ የትኛውም ሀይማኖት እረፍት አይኖረውም። ሀገር ሰላሟ ተነስቶ ከገደል አፋፍ ቆማ ተደላድለን የተቀመጥን ከገደል አፋፍ ላይ ካለችው ሀገር ውስጥ ነንና አንድ የሚያደርገንን መንገድ መርጠን ልዩነታችንን አጥበን ሀገራችንን እናድን። ለዚህም ነው፣ "ለፍቅሩም ለጠቡም እስኪ መጀመሪያ ሀገር ትኑር..." የምለው:: አበቃሁ፤ ሰላም!

# የዘመንና የፋሽን ትስስር

**ተገኝ ብሩ**

የፋሽን ዋንኛ መገለጫ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ወቅታዊነቱ ነው። ወቅትን እየጠበቁ ሽክ ማለት፣ የአየር ሁኔታንና ተለምዷዊ ጉዳዮችን በማገናዘብ በፋሽን መድመቅ የዘመነኞች የተለመደ ተግባር ነው። እከሌ ፋሽን ተከታይ ነው፣ እገሊት ከፋሽን ጋር ቅርበት አላት የሚባልላቸው ግለሰቦች ወቅትንና ሁኔታን ያገናዘበ አልባሳትን በማዘውተራቸው ነው።

ወቅትን እየጠበቁ ሽክ! ማለት ዛሬ ላይ በስፋት ተለምዷል። ዘመነኞች የዘመናቸውን ግኝቶች፣ ቴክኖሎጂ የፈጠረላቸውን ጥበብ ተጠቅመው በሁሉም የአየር ንብረት ውስጥ በምቾት ሽክ ብለው መታየት እንዲችሉ የሚያደርጓቸውን አልባሳትና መጫሚያዎች ይጠቀማሉ። እንደ አየሩ ጸባይ ለብሶ ማጌጥና መዘነጥ ዛሬ ላይ በብዙዎች ዘንድ ተለምዷል። የሚዘወተር ተግባርም ነው። የክረምት ወቅትን ደረብረብ አድርገን ብርዱን የተከላከልንበት ወፍራም ገበር ያለውና ሙቀትን የሚጠብቅ ልብስ ክረምቱ አልፎ የፀደይ ወቅት ብቅ ሲል መቀየር ያስፈልገን ይሆናል። ይህንን ማድረጋችን ባናውቀው እንኳን ከፋሽን ባህሪያት አንዱን በመተግበራችን ፋሽን ተከታይ ሊያደርገን ይችላል።

ፋሽን ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ባሟላ መልኩ ሲገኝ ተቀባይነቱ ከፍ እንደሚል ይነገራል። የተጠቃሚዎች ምቾት ውበትንና ዲዛይን ለፋሽን ዋንኛ ጉዳዮች ናቸው። የዘርፉ ባለሙያዎች የሚስማሙት እነዚህ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ፋሽንን ፋሽን የሚያደርጉ መሆናቸውን ነው። እነዚህ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ደግሞ ሌላ ወሳኝ ጉዳይ ታሳቢ አድርገው ይበጃሉ። እነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች ከሚገኙበት ወቅት ጋር ካልተጣጣሙ የፋሽን ሙሉዕነትን እንደሚያጎድሉ የምትናገረው ዲዛይነር ዳናይት ሳህሉ፤ ወቅት ወይም ዘመን ከፋሽን ጋር ያለውን ከፍ ያለ ቁርኝት ታብራራለች። ከሶስት ዓመት በላይ በፋሽን ዲዛይነርነት ከሁለት ዓመት በላይ ደግሞ በሜካፕ አርቲስትነት ሙያ ለቆየችው ዳናይት ፋሽን ከወቅት ጋር የማይነጣጠል አንዱ በአንዱ ውስጥ የሚከሰትና የተሳሰረ መሆኑን ትገልፃለች።

ሰው ዘመኑን ይመስላል። ይህ ፋሽን የዚህ ዘመንና ወቅት ነው፤ ያኛው ደግሞ የዚያኛውን ዘመን ያስታውሰናል የምንለው በጊዜና በሁነት ውስጥ ተከስቶ ያለፈና የተለወጠ ሂደት በመኖሩ ነው። ድሮ አባቶች የፈሸኑበት ተነፋነፍ በዚያ ዘመን አምረው ደምቀው 'ዋው' የተሰኙበት ነበር። ዛሬ የዚህ ዘመን ወጣት አንስቶ ቢለብሰው ምን አልባትም ያን ዘመን ለማሳብ ለበሰው አልያም ታሪክን ለማውሳት አጠለቀው ቢባል እንጂ ከዘመኑ ጋር ስለተላለፈ በተመልካቾች አልያም በዚህ ዘመን ወጣቶች ብዙም ትኩረት ላይስብ ይችላል። የዛሬ ሲኪኒ ሱሪዎችን አልያም አሁን ላይ በወጣቶች የሚዘወተሩ አለባበሶችን ወደ ኋላ መልሰን ለአባቶች የማቅረቡ እድል ቢገጥመን የሚሰጡት አስተያየት ያልተጠበቀ ሊሆን ይችላል።

ከላይ የተገለፁትና ፋሽንን ፋሽን ከሚያሰኙት ጉዳዮች በተጨማሪ በፋሽን እሳቤ ውስጥ ታሳቢ የሚደረገው ወቅታዊነት የፋሽን ትልቁ ጉዳይ ነው። ለክረምት ዲዛይን የተደረገ በጋ ላይ ምቾት ሊፈጥር ከቶም አይችልም። በጋ ላይ ሊለበስ በፍካቱ የተመረጠ አልባስ ክረምት ላይ በዝናብና በጭቃ ለመልበስ ይቸግር ይሆናል።

ለፋሽን ቅርብ የሆኑ ባለሙያዎች የፋሽንን ትርጓሚ ከዚህ ባያርቁትም ከዘመኑ ጋር የታረቀ ጊዜውን የሚመስል፣ ተለብሶ የሚያምር፣ ለለባሹ ምቾት የሚሰጥ አለባበስ ሁሉ ፋሽን እንደሚሰኝ ይገልፃሉ። ዲዛይነር ዳናይት ሳህሉ የፋሽን ትርጓሜው ሰፊና ጥልቅ እንደሆነ ትገልፃለች። አንድ ልብስ ወይም መገልገያ ፋሽን የሚያስብለው ግን የተገኘበት ዘመንና በተጠቃሚዎች ተቀባይነት ማግኘቱ ዋንኛው ጉዳይ እንደሆነ ታስረዳለች። መገልገያው አልያም ልብሱ ፋሽን የሚያሰኘው ደግሞ ከላይ በተገለፁ ሶስት ዋንኛ ጉዳዮች መለኪያነት መሆኑን ታስቀምጣለች።

**ፋሽን ሲታሰብ ከንድፍ ጀምሮ ፋሽኑ የተፈጠረበት ዘመን የማህበረሰብ አስተሳሰብና ባህል፣ ፋሽኑ የተፈጠረበት ወቅትና ቴክኖሎጂ፣ የማህበረሰቡ ወይም የሆነ ቡድን ምርጫና የአየር ሁኔታን መሰረት ያደርጋል**

ሰው በተገኘበት ዘመን ላይ የሚገኝን የአለባበስ ባህል እና ስርዓት ተከትሎ አካባቢውንና ማህበረሰቡን መስሎ በብዙዎች የተመረጠና የተወደደ እንዲሁም ምቹ የሆነ የፋሽን ግብዓትን ይጠቀማል። ይህ ደግሞ ይሰፋና በብዙዎች የሚዘወተር ይሆናል። ያኔ የወቅቱ ፋሽን ሆኖ ይተገበራል፤ ተቀባይነትም ያገኛል። ወቅቱን ጠብቀን የምንጫማው አልያም ገዝተን የምንለብሰው ልብስ አስበን ወይም በአጋጣሚ ብናደርገው መለኪያውን በማሟላቱ ፋሽን ይሰኛል፤እኛም የፋሽን ተከታዮች አልያም ተጠቃሚዎች ሆንን ማለት ነው።

የፋሽን ዲዛይነሯ ሀና መኮተ የፋሽንና ዘመን ቁርኝትን እንዲህ ትገልጸዋለች "ፋሽን ሊሰኝ የሚችል አልባስ ወይም መገልገያ የሆነ ዘመን ላይ የተወደደና ፋሽን ተደርጎ በብዙዎች የተወደደን በሌላኛው ዘመን ላሉ ፋሽን ተከታዮች እጅጉን የሚያስገርም ሊሆን ይችላል"። ምክንያቱም ፋሽን ሲፈጠር ዘመንና የማህበረሰቡን አጠቃላይ ሁኔታ መሰረት አድርጎ መሆኑ ታስረዳለች። ፋሽን ከዘመን ጋር የተገናኘ እሳቤና ትግበራ ውጤት መሆኑንም ታምናለች። ለዚህ ነው ብዙውን ጊዜ አልባሳት ላይ አስተያየት ሲሰጥ "ይህ እኮ ፋሽኑ አልፎበታል" እየተባለ በብዙዎች የሚነገረው። ይህ ነው የፋሽን ወቅታዊነት ትልቁ ማሳያም። ፋሽን ከተገኘበት ዘመን እና የአየር ንብረት ጋር ታርቆ ካልቀረበ ቀጣይነቱ ጥያቄ ውስጥ ይገባል።

ወቅታዊነት የፋሽን ዋንኛ ባህሪው ነው። ለዚህም ነው ፋሽን የተገኘበት ዘመን አሻራ ሆኖ፤ የተፈጠረበትና የተዘወተረበት ጊዜ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰደው። አንድ ወቅት ላይ የነበረ ፋሽን ያንን ወቅት ተሻግሮና ተረስቶ ከዘመናት በኋላ ፋሽንነቱ ያልፍና በሌላኛው ዘመን "ያኔ ይዘወተር የነበረ " ተብሎ ፋሽኑ እንደ ታሪክ ይነገራል። ለዚህም ነው የፋሽንና ዘመን መተሳሰር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ሆኖ ጎልቶ የሚታየው።

ፋሽን ሲታሰብ ከንድፍ ጀምሮ ፋሽኑ የተፈጠረበት ዘመን የማህበረሰብ አስተሳሰብና ባህል፣ ፋሽኑ የተፈጠረበት ወቅትና ቴክኖሎጂ፣ የማህበረሰቡ ወይም የሆነ ቡድን ምርጫና የአየር ሁኔታን መሰረት ያደርጋል። በተለይም ቦታ፣ ጊዜና የአየር ሁኔታ ለፋሽን አልባሳት ዕውን መሆን ወሳኝ ቅድመ ሁኔታዎች ሆነው ይቀመጣሉ።

ፋሽኑ ልብስ ቢሆን ባለሙያው ከዘመኑ ሰዎች ፍላጎትና ተለምዶ በተጨማሪ በምን አይነት ቦታ ላይ ይለበሳል? የሚለው ጉዳይ ያሳስበዋል። ዘወትር፣ የበዓል ቀን አልያም ሁነቶችን መሰረት ሲያደርግ በምን አይነት ጊዜና ወቅት የሚለው ደግሞ ቀን፣ ማታ፣ፀደይ፣ በጋ ክረምት የመሳሰሉት እንደ አየር ንብረቱና ወቅቱ የሚለበሱትን ልንጠቅስ እንችላለን። ይህን ባገናዘበ መልኩ ተዘጋጀ ፋሽን ሁለንተናዊ የፋሽን መሰረታዊ ጉዳዮች አሟልቷልና ፋሽን ይሰኛል። ይህም ከዘመን ጋር የታረቀ በተገኘበት ዘመን የተወደደ ፋሽን ሆነ ማለት ነው።

## ማረፊያ/ትዝብት

# መጀመሪያ ለስሙ መገለጫ እንስጠው

**አቤል ገብረኪዳን**

ሰሞኑን ማህበራዊ ሚዲያው በአማራ ክልል በሚካሄደው ዘመቻ ዙሪያ ባለ ክርክር ተወጥሮ ከርሟል። መንግስት ዘመቻው ህግን የማስከበር ነው ሲል ይህን የሚቃወሙ ሀይሎች ደግሞ መንግስት የያዘው ፋኖን ማሳደድ እና ትጥቅ ማስፈታት ነው የሚል ክርክር ያነሳሉ። በመንግስት በኩል የክልሉ አስተዳደር ይህን ይቃወማል። የክልሉ የኮሚኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ሙሉነህ እንደሚሉት ከሆነ ዘመቻው እየተካሄደ ያለው ፋኖ ላይ ሳይሆን በፋኖ ስም በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ ነው። "ሥርዓትና ሕግ የሚያከብሩ፣ የተጋደሉ፣ የተዋጉ ፋኖዎች አሉ፣ በእነዚህ ስም መነገድ አይቻልም፣ ማህበረሰቡ ለጀግና ፋኖዎች የሚሰጠው ክብር ይታወቃል፣ ፋኖነትን ከደሙ ጋር ያዋሀደ ጀግና ሕዝብ ነው፣ እስር ቤት ጥሶ ወንጀለኛን ያስለቀቀ ቡድን ላይ እርምጃ ስትወስድ ፋኖን ትጥቅ ሊያስፈታ ነው ይልሃል፣ ይሄ የፋኖ መገለጫ አይደለም፤ ይሄ ትልቁን ክብራችን የማዋረድና የመናቅ ነው" ብለዋል አቶ ግዛቸው።

ከዚህ የኃላፊው ንግግር በመነሳት የምናነሳው አንድ ጥያቄ አለ። ፋኖ ማን ነው? ይህ ጥያቄ ቀጥሎ ለሚኖሩ ውይይቶች ወሳኝ ነው። ፋኖ ለምንለው ሀይል የምንሰጠው መገለጫ (characteristics) ከዚያ ሀይል ጋር ለሚኖር መስተጋብር ያለው ፋይዳ ወሳኝነቱ የጎላ ነው። ይህ ግን ለፋኖ ብቻ ሳይሆን ለቄሮም ፤ ለዘርማም፤ ለሌላውም የሚሰራ ነው። እነዚህ ቡድኖች ማናቸው? ምንድን ነው መገለጫቸው? የሚለውን ከለየን በኋላ ነው የልማት ወይም የጥፋት ሀይሎች ናቸው የሚለውን የምንበይነው። በዚህ መልኩም ነው ሕወሓት እና ኦነግ ሸኔ የሽብር ቡድን ተብለው የተሰየሙት እና እርምጃ እየተወሰደባቸው ያለው።

አሁን ላይ ፋኖ ነኝ ፤ ቄሮ ነኝ ፤ እገሌ ነኝ የሚል ሰው ብዙ ነው። በዚህም የተነሳ እነዚህ ስሞች የብዙ የተለያየ አጀንዳ ያላቸው ሀይሎች መሰባሰቢያ ሆነዋል።ይህ ብዙ ችግር እያስከተለ ነው። ሁሉም የልቡን ከፈጸመ በኋላ ሲያዝ ፋኖ ስለሆንኩ ተያዝኩ ፤ ቄሮ ስለሆንኩ ተጎዳሁ እያለ ህዝብ ማወናበዱን ተያይዞታል። ስለዚህም ፋኖ ማለት ይህ ነው ፤ እንዲህ አይነት ባህሪ ያለው ፤ ይህን የሚያደርግ ይህን ደግሞ ፈጽሞ የማያደርግ ፤ በዚህ ቦታ የሚገኝ በዚያ ቦታ ደግሞ የማይገኝ ፤ እንዲህ የሆነ እና እንደዚያ ያልሆነ ነው ተብሎ የማንነት መገለጫ ሊሰጠው ይገባል። በዚህ መልኩ ፋኖን ከተራ ወንበዴ መለየት ይቻላል።በተመሳሳይም ለቄሮም እንዲሁ።ለዘርማም እንዲሁ።ለሌላውም እንዲሁ።

**የመጀመሪያው ፋኖ የልማት እና የሰላም ሀይል ነውና ድጋፍ ሲደረግለት የሚገባ ሲሆን ሁለተኛው በአንጻሩ በፋኖ ስም የሚንቀሳቀስ ወንበዴ ነውና እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል**

ከላይ እንዳልኩት መገለጫዎችን ማውጣት መቻል ከአላስፈላጊ ትርምስ ለመዳን ያግዛል። ለምሳሌ ያህል በአንድ ወቅት ላይ ልማታዊ ባለሀብት የሚል ብያኔ ተፈጥሮ ነበር።ይህ ስያሜ ስራቸውን በአግባቡ ለሚሰሩ፤ ጉቦ ለማይሰጡ ፤ ግብር በሰአቱ ለሚከፍሉ ፤ ህገወጥ የገበያ ውድድር ለማይፈጥሩ፤ ኢኮኖሚያዊ ሳቦታጅ ላይ ላልተሰማሩ ባለሀብቶች የሚሰጥ ስም ነበር። እነዚህ ባለሀብቶች የመንግስት ጥበቃ የማይለያቸው እና የልማት ቅድሚያ የሚሰጣቸውም ናቸው። ይህ ማለት ከነዚህ በተቃራኒ የሆኑ ባለሀብቶች አሉ ማለት ነው። ልማታዊ ባለሀብት የሚለው መጠሪያ እና መገለጫዎቹ በእርግጥም ጠቀሜታ አላቸው። አንደኛ ሁሉም ባለሀብት ሌባ ነው ወይም ሁሉም ባለሀብት ሀብቱን በልፋት ነው ያገኘው ከሚል ስህተት ለመዳን እና ባለሀብትን ሁሉ በአንድ አይን ላለማየት ያግዛል። ሁለተኛ ከመልካሞቹ ባለሀብቶች ጋር የሚደረገውን ውይይት በበጎ ለመቃኘት ከአስቸጋሪዎቹ ባለሀብቶች ጋር የሚደረገውን ውይይትም ቆምጠጥ ለማድረግ ያስችላል። ሶስተኛው እና ዋነኛው ግን መንግስት ማንን እንደ አይኑ ብሌን ማየት እንዳለበት ማንን ደግሞ በአይነ ቁራኛ መከታተል እንዳለበት ለመወሰን ያስችላል።

ወደ ፋኖ ጉዳይም ሲመጣ በተመሳሳይ መታየት ያለበት ጉዳይ አለ። ትክክለኛው ፋኖ ማን ነው? በፋኖ ስም የሚነግደው ወንበዴስ ማነው? የሚለውን መለየት ያስፈልጋል። ትክክለኛው ፋኖ ቅድሚያ ለህዝብ የሚሰጥ ፤ በጦርነት ወቅት በጀግንነት የሚዋጋ ፤ በሰላም ቀን ተግቶ የሚያርስ የሚነግድ ፤ ትዳር እና መኖሪያ ያለው ፤ መንፈሳዊ እና ማህበራዊ ግዴታውን በቅጡ የሚወጣ ፤ ህግን የሚያከብር ፤ የጎበዝ አለቃነት ስሜት ያልተጠናወተው ፤ ለአላማው እንጂ ለስልጣን እና ለጥቅም የማይሞት ወዘተ... መሆን ያለበት ነው። በተቃራኒው ህጻናትን አግቶ ገንዘብ የሚጠይቅ ፤ ሴቶችን የሚደፍር ፤ ወንዶችን የሚገድል ፤ ቤት አልባ አውደልዳይ ፤ ህግ የማያከበር ፤ ስራ መስራት የማይወድ ፤ መሳሪያው ከትከሻው የማይወርድ ፤ ህገወጥ መሳሪያ እና ገንዘብ የሚያዘዋውር ፤ ባለሀብቶችን እንዳይሰሩ የሚያደናቅፍ፤ የጎበዝ አለቃ የመሆን አላማ የያዘ ፤ በጎጥ የታጠረ ፤ ከጠላቶች ጋር ለጊዜያዊ ጥቅም የሚያብር እሱ ደግሞ ፋኖ ሳይሆን በፋኖ ስም የሚመጣ ወንበዴ ነው። ስለዚህም በዚህ መሰረት የመጀመሪያው ፋኖ የልማት እና የሰላም ሀይል ነውና ድጋፍ ሊደረግለት የሚገባ ሲሆን ሁለተኛው በአንጻሩ በፋኖ ስም የሚንቀሳቀስ ወንበዴ ነውና እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል።

በእርግጥ እስካሁን እንዳየነው ከሆነ የአማራ ክልልም በዚህ መሰረት እየተጓዘ ይመስላል። ትክክለኛ የሰላም ሀይል ናቸው እውነተኛ ፋኖ ናቸው ያላቸውን ሸልሟል። ከሽልማቱ በኋላ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን "ልዩ ኃይል፣ ሚሊሻ እና ፋኖ የአይበገሬነት እና የአትንኩኝ ባይነት ተምሳሌቶች ናቸው! በማለት የፋኖ መገለጫ አይበገሬነት እና አትንኩኝ ባይነት እንደሆነ ተናግረዋል። ስለዚህም ክልሉ ሰላማዊ የሚላቸውን ፋኖዎች ለይቷል፤ መገለጫቸውንም በይፋ ማለት ነው። ይህ ከሆነ ዘንድ ክልሉ ቀጣይ ተግባሩ መሆን ያለበት ይህን የትክክለኛ ፋኖ መገለጫ ለህዝቡ ማሳወቅ ሲሆን፤ በፋኖ ስም የሚንቀሳቀሰውን ወንበዴም የማጋለጥ ተግባር በአግባቡ ሊሰራ ይገባል። ይህ ስራ ከተሰራ ህዝቡ ፋኖ ስለሆንኩ ታሰርኩ በሚል ማወናበጃ አይሳሳትም ማለት ነው። ትክከለኛው ፋኖ መገለጫው ከታወቀ ያ ሰው እኔ ፋኖ ነኝ ባይል እንኳ ህዝቡ ስራውን አይቶ ያውቀዋል፤ ይደግፈዋል። በተቃራኒው ፋኖ ሳይሆን ፋኖ ነኝ የሚለውንም ወግድ አንተ ወንበዴ ነህ ማለት ይችላል።

ስንጠቀልለው ክልሉ ፋኖ ለሚለው መጠሪያ መገለጫውን ሊያበጅለት እና ህብረተሰቡን ቀድሞ ሊያሳውቅ ይገባል። ያኔ ህዝብ ከመንግስት ጎን በመሆን የሰላም አጋር መሆን ይችላል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ሀገር እና ደጋግ ልቦች...

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዛሬ ወቅታዊ ከሆኑ ጉዳዮቻችን መካከል አንዱ የሆነውን የኑሮ ውድነት በማስመልከት 'ሀገርና ታማኝ ልቦች ስል በአዲስ ሀሳብ መጥቻለው። ጽሁፌን በጥያቄ መጀመር እፈልጋለው ‹ለእናንተ ኢትዮጵያዊነት ምንድነው? በዚህ ታላቅ ጥያቄና መልስ ውስጥ ራሳችሁን አስቀምጣችሁ ተከተሉኝ። ሀገር የታማኝ ልቦች ነጸብራቅ ናት። ከጥንት እስከዛሬ ኢትዮጵያን የሳሉ እጆች ክፉ ሆነው አያውቁም። ኢትዮጵያን የደገፉ ክንዶች ራስ ወዳድ ሆነው አያውቅም። ኢትዮጵያዊነት ርህራሄ ነው። አለም ላይ ስለሌላው የሚያዝኑ ልቦች፣ ስለሌላው የሚያነቡ አይኖች ኢትዮጵያዊ ናቸው። በዚህ ተፈጥሮአዊ ባህሪያችን ውስጥ በርካታ አስቸጋሪ የሚባሉ ጊዜአትን በጋራ አሳልፈናል።

ኢትዮጵያዊነት ሲነሳ ሁሉንም የሚያስገርም አንድ የጋራ እውነት አለን፤ እርሱም ተካፍሎ የመብላት ባህላችን ነው። ለናሙናነት ይሄን አነሳሁ እንጂ ኢትዮጵያዊነት ሲገለጥ አብረው የሚገለጡ በርካታ የአብሮነት ታሪኮች ያሉን ህዝቦች ነን። ይሄ እኔና ሌላውን አለም የሚያስደንቀን ጥልቅ..ምጥቅ እሴታችን ነው። በዚህ ባህላችን ብቻ ከአለም እና ከታሪኳ ልዩዎች ነን። አለም እኔነትን ባስቀደመበት፣ ብቻ መብላትን እንደ ስልጣኔና እንደ ዘመናዊነት በያዘበት በዚህ ዘመን ላይ እኛ ኢትዮጵያዊያን ግን በጋራ በመቆም፣ በጋራ በመብላት የማንነጣጠል ህዝቦች መሆናችንን ስናሳይ ኖረናል..እያሳየንም እንገኛለን።

ይህ በየትኛውም የአለም ክፍል የሌለ የሚያኮራና የሚያስደንቅ ኢትዮጵያዊ መልክ ነው። ይህ ለሰው ልጅ ክብር የሰጠ፣ አንድነትን ያስቀደመ የስልጣኔ አሻራ ነው። ይህ የእኛ ብቻ የሆነ የድንቅ ስርዐት ውጤት ነው። ይህ የኢትዮጵያን ቀደምት ስልጣኔና የአብሮነት መንፈስ የሚገልጥ ሰነድ ነው። ሁሌም እንደምለው ስልጣኔ ራስን ከመውደድና የራስን እውነት ከመቀበል የሚጀምር ነው። ሁሌም እንደምለው ዘመናዊነት ከራስ እውነት ተነስቶ ወደ ሌሎች የሚተላለፍ የአስተሳሰብ ውጤት ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ቀደምት ስልጡን ህዝቦች ስለመሆናችን በርካታ ማስረጃዎች አሉ። ይሄ ሁሉ ባይሆን እንኳን አብሮ መብላታችን፣ አብሮ መቆማችን በደስታና በሀዘናችን ጊዜ መረዳዳታችን ቀዳሚነታችንን ከማሳየቱም በላይ የስልጣኔ ፈር ቀዳጆች እንደሆንን አንዱ አመላካች እውነታ ነው።

አሁንም የጥንቱን ሀያልነታችንን ይዘን እንቀጥል ዘንድ በዚህ ፈታኝ ጊዜ ላይ በመደጋገፍና በመረዳዳት አለኝታነታችንን ማሳየት ይኖርብናል። ኢትዮጵያዊነት የሚያምረው በመስጠት ነው። በመስጠት የከበረች ሀገር በስስት መርከስ የለባትም። አብሮ በመብላት የቆመች ሀገር ለኔ ብቻ በሚል ሴይጣናዊ አስተሳሰብ ልዕልናዋን ማጣት የለባትም። እንዳማረብን በአባቶቻችን የደግነት መንፈስ ወደ ፊት መጓዝ ነው የሚያዋጣን። ይህ ጊዜ በኑሮ ውድነት ህዝባችን የሚሰቃይበት ጊዜ ነው። ያለው በመስጠትና በማካፈል አጋርነቱን ሊያሳይ ይገባል።

ሰው ብዙ እውቀት፣ ብዙ ጥበብ፣ ብዙ ማስተዋል ሊኖረው ይችላል ሌላውን እንደማፍቀር፣ ለሌላው እንደ ማሰብ ግን እውቀት አይኖረውም። ሰው ብዙ በጎ ስብዕናዎች ሊኖሩት ይችላሉ፤ ሀገርን እንደመውደድና ለወገን ተቆርቋሪ እንደመሆን በጎ ስብዕና አለው አልልም። ይህ የታማኝና የእውነተኛ ሰውነት መገለጫ ባህሪ ነው። ሀገራችን ደግሞ ከትላንት እስከዛሬ በዚህ እውነት ውስጥ የኖረች ናት። እኔ መስጠትን የክብር ሁሉ ዘውድ፣ የጥበብ ሁሉ ምንጭ እለዋለው። እኔ በግሌ እንደ ኢትዮጵያዊነት ጥያቄና መልስ አላውቅም.. እርግጠኛ ነኝ እናተም አታውቁም። ብዙ እውቀት፣ ብዙ ጥበብ፣ ብዙ ማስተዋል ሊኖረን ይችላል፤ እንደ ሀገርና ሰው፣ እንደ ታሪክና ባህል፣ እንደ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ጥበብና ማስተዋል ግን የለንም.. አይኖረንምም።

እንግዲህ ይቺን ነው ኢትዮጵያ የምላችሁ። ይሄን ነው ኢትዮጵያዊነት የምላችሁ። ይሄን ነው ሀገርና ታማኝ ልቦች ስል የማወጋችሁ። ከነገርኳችሁ በላይ የምታውቁት ሀቅ አለ? ከሀገርና ሰው በላይ ምን ጥበብ ምን ልህቀት አላችሁ? ከዚህ እውነት በመነሳት የሰሞኑን ከኢትዮጵያ ባህልና አብሮነት ያፈነገጠውን ሰሞነኛ እውነት ላውጋችሁ። የሰሞኑ የኑሮ ውድነት ያላማረረው ማነው? እርግጠኛ ነኝ ሁላችሁም ተማርራችኋል። ከመማረርም ባለፈ የብዙዎቻችንን ህልውና የፈተነ እንደነበር እኔም እናተም ምስክሮች ነን። ይሄ እንዴት ሆነ? በማን ሆነ? ለምን ሆነ? ብለን ስንጠይቅ መልሱን እናገኘዋለን።

**ለድሀ እየሰጡ እንጂ ከድሀ እየነጠቁ ማደግና መበልጸግ አይቻልም። ለድሀ ቸርነትን እያደረጉ እንጂ በድሀ ላይ በመጨከን ነገን ማየት አይቻልም። እድገት ያለው በመስጠትና በቸርነት ውስጥ ነው። ሀብትና በረከት የሚመጣው ለድሀ ቸርነትን በማድረግ እንጂ ድሀን በማስጨነቅ አይደለም። አካሄዳችንን እናስተካክል። ስራችን በእውነትና በእውቀት ህዝብን ማዕከል ያደረገ ይሁን**

እንደነገርኳችሁ እንደምታውቁትም ኢትዮጵያዊነት ተካፍሎ መብላት ነው። ኢትዮጵያዊነት የታማኝ ልቦች አብራክ ነው። በዚህ እውነት ውስጥ ተወልደንና አድገን ነገር ግን በደጋግ ልቦች መሀል በበቀሉ የክፋት ልቦች የድሮ ጸዐዳ መልካችንን እያጣን ነው። ክፋትንና እኔነትን በለመዱ፤ ሌብነትንና ስግብግብነትን በተማሩ አንዳንድ ነጋዴዎች የጥንት ፍቅራችንን እየተነጠቅን ነው። ራስ ተኮር የሆኑ ወጪት ሰባሪዎች ሆን ብለው የኑሮ ውድነትን በመፍጠር በህዝቡ ላይ ግፍና በደልን እየሰሩ ነው። በተለይ ድህው ማህበረሰብ በእነዚህ ውሸታምና አጭበርባሪ ነጋዴዎች እየተሰቃየ ያለበት ሁኔታ ጎልቶ ይታያል።

ይሄ ብቻ አይደለም የወቅቱን አስቸጋሪነት እንደ መልካም እድል በመጠቀም ድሀ አስጨንቀው በአቋራጭ ለመበልጸግ የሚሹ ሀላፊነት የማይሰማቸው ነጋዴዎች እንደ አሸን እየፈሉ ነው። ህዝብ ከማገልገል ይልቅ ያልተገባ ትርፍና ጥቅም ለማግኘት በሸቀጦች ላይ ያልተገባ የዋጋ ጭማሬ በማድረግ ጊዜውን ፈታኝ አድርገውታል። ምርት በመደበቅ፣ በማሸሽና ሌሎች ማጭበርበሪያ መንገዶችን በመጠቀም ከመንግስት እውቅና ውጪ በሆነ አሰራር ራሳቸውን ሲጠቅሙና ድሀ ህዝብ ሲበዘብዙ ማየት አዲስ ነገር አይደለም። ወቅታዊውን አለም አቀፍ ችግር እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ሀብት ለማጋበስና የኑሮ ውድነትን በመፍጠር መንግስትና ህዝብን ሆድና ጀርባ ለማድረግ እየሰሩ ያሉ የክፉ ልቦች እዚም እዛም ተሰግስገው ይገኛሉ። የነዚህ ግለሰቦች ስውር አላማ የታወቀ ነው፤ እናም በአንድ ላይ ሆነን እኚህን ህገ ወጦች በማጋለጥና ለህግ በማቅረብ የኑሮ ውድነቱን ማስተካከል የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

ለዘመናት አብሯቸው የኖረን ህዝብ በማገዝና በመደገፍ በዚህ ክፉ ቀን ላይ ውለታውን እንደመመለስ ዞሮ ጨካኝ መሆን ውለታ ከመብላት ባለፈ ነውረኛ ድርጊት ነው። አብረው የማይኖሩ ይመስል..ይሄ ክፉ ቀን የማያልፍ ይመስል እንዲህ አይነት ያልተገባ ግፍ መስራት ተገቢ ነው ብዬ አላምንም። ይሄ ጊዜ ያልፋል፤ ሁላችንም የምንናፍቀው አዲስ ቀን ይፈጠራል፤ በዚህ የንጋት ዋዜማ ላይ እንደ አባቶቻችን ስርዐት እርስ በርስ መተጋገዝ እንጂ ሆድና ጀርባ መሆን የለብንም። ይህ የኢትዮጵያዊነት መልክ አይደለም። ይህ ከአባቶቻችን የወረስነው የክብር ዘውድ አይደለም። ይህ ነውር ነው። ይህ በሰዎች መከራ ራስን የማኖር ሰይጣናዊ እሳቤ ነው። ይህ ኢትዮጵያዊነትን የሚያደበዝዝ የራስ ወዳድነት ስብዕና ነው። በዚህ ስርዐት ውስጥ አልመጣንው። ይሄን የጭካኔ ተግባር አናውቀውም። ስርአታችን አብሮ መብላት፣ አብሮ መጠጣት ነው። ስርዐታችን ተካፍሎ መብላት ነው፤ ያለው ለሌለው መስጠት ነው። ስርዐታችን እንደ አብረሀም ቤት በራችንን ከፍተን ለደግነት መንገደኛ የምንጠብቅ፣ ርሀብተኛ የምናጠግብ፣ የታረዘ የምናለብስ መሆኑ ላይ ነው። ነውር የምናውቅ ህዝቦች እኮ ነን፤ ይህስ የት ሄደ? ድሀን እንደማስጨነቅ፣ ከድሀ ላይ እንደመውሰድ እኮ ግፍና በደል፣ ሀጢያትና ነውር የለም። አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ድሀ ነው፤ የሰሞኑ የነጋዴዎቻችን ሁኔታ ከዚህ የዘለለ አይደለም።

ለድሀ እየሰጡ እንጂ ከድሀ እየነጠቁ ማደግና መበልጸግ አይቻልም። ለድሀ ቸርነትን እያደረጉ እንጂ በድሀ ላይ በመጨከን ነገን ማየት አይቻልም። እድገት ያለው በመስጠትና በቸርነት ውስጥ ነው። ሀብትና በረከት የሚመጣው ለድሀ ቸርነትን በማድረግ እንጂ ድሀን በማስጨነቅ አይደለም። አካሄዳችንን እናስተካክል። ስራችን በእውነትና በእውቀት ህዝብን ማዕከል ያደረገ ይሁን። እኛ ስንሰጥና ስናካፍል እንጂ ስንዘርፍና ስናታልል አልኖርንም። እኛ በጋራ በመብላት በጋራ በመኖር እንጂ በውሸትና በማጭበርበር ራሳችንን ብቻ ስንጠቅም አልኖርንም። እኛ የሌላውን ጎደሎ በመሙላት ተያይዘን የመጣን ህዝቦች ነን ይሄን ኢትዮጵያዊ እውነት አትሳቱ። በዚህ ክፉ ጊዜ ላይ እንደ ባህላችን ለችግረኞች ልባችንን በመክፈት ይሄን ክፉ ጊዜ በጋራ መሻገር ይኖርብናል። ካልተጋገዝን የምንራመደው የብቻ መንገድ የለም። መንገዶቻችን ሁሉ በጋራ ተራምደን በጋራ የመጣንባቸው ናቸው። በእኔነት ስሜት የምንገነባው የብቻ መንገድ እኛን ከመጣል ባለፈ እርባና የለውም። እንደ አባቶቻችን በጋራ እየበላን በጋራ መኖር ነው የሚያዋጣን። እንደ አባቶቻችን በጋራ ሀሳብ የጋራ ስርዐት መገንባት ነው የሚጠቅመን።

ሰው ሀገር እንደሚፈልግ ሁሉ ሀገርም ሰው የምትፈልግበት ጊዜ አለ። ሀገር ሰው የምትፈልግበት ትክክለኛ ጊዜ ደግሞ አሁን ነው። ለዘመናት በሀገራችን ላይ ተዘባንነን ኖረናል። በህዝባችን ፍቅር ለዘመናት ታቅፈን ሳይበርደን ከትላንት ዛሬን አይተናል። አሁን ጊዜው በአንድነት መንፈስ ሀገር የምናቆምበትና በመረዳዳት መንፈስ ወገን የምንታደግበት ነው። ኮሮና ይዞት የመጣው ብዙ ነገር አለ። ከኮሮና ሳናገግም የሰሜኑ ጦርነት ተከሰተ። በሰሜኑ ጦርነት ተጎሳቁለን ሳይበቃን፤ ተጽዕኖው የኑሮ ጫናችንን ያከበደው የሩሲያና የዩክሬን ጦርነት ተከተለ። በዚህ ሁሉ ውስጥ ነን። ህዝባችን ከመቼውም ጊዜ በላይ በውስጥም በውጪም በተነሱ ችግሮች በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ይገኛል። በዚህ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ለሚኖር ማህበረሰብ የእኛ ፍቅር፣ የእኛ ደግነት ዋጋው ምን ያክል እንደሆነ ለመገመት አይከብድም። እጆቻችን የሚሰጡበት፣ ልቦቻችን የሚያዝኑበት ሰሞን ላይ ነን። በደግነት ፈጣሪን የምናስደስትበትና የጽድቅ ስራ የምንሰራበት ሰሞን ላይ ነን። እንደ ሀገር ድሀ ነን፣ እንደ ህዝብ ደግሞ ችግረኛ። ከላይ የዘረዘርኳቸው ማህበራዊ ቀውሶች ተጨምረውብን ደግሞ የሚሆነውን አስቡት። እመኑኝ ካልተሳሰብን ይሄን ጊዜ አናልፈውም፤ አዲስ የተስፋ ማለዳ እናይ ዘንድ ልቦቻችንን ለሌላው ማራራት ይኖርብናል።

እንዘን ካልን የምናዝንላቸው ብዙ የማህበረሰብ ክፍሎች አሉ። በኑሮ ውድነቱ ሳቢያ ወርሀዊ ደሞዛቸው የወር አስቤዛ የማይገዛላቸው፣ ቤት ኪራይ ለመክፈል ያልቻሉ ብዙ ወገኖች በዙሪያችን አሉ። መማር እየፈለጉ በብዙ ምክንያት መማር ያልቻሉ፣ መለወጥ እየፈለጉ በአቅም ማነስ ወደ ኋላ የቀሩ ብዙ ናቸው። ለነዚህ ወገኖቻችን አለኝታነታችንን ማሳየት ይጠበቅብናል። ሰው ልቡ ቀናነትን ከተላበሰ የሚሰጠው አያጣም። መስጠት ሁልጊዜ ከኪስ አውጥቶ መስጠት አይደለም። ከኪሳችን ስናጣ ከልባችን የምንሰጠው ብዙ ነገር አለ። ከኪስ ይልቅ የልብ ስጦታ ተቀባይን ይባርካል ብዬ አምናለው፡ ኪሳችን ሲራቆት ብቻ ሳይሆን ኪሳችን በሞላ ጊዜም የልባችን ኳዳ መፈተሸ አለብን እላለው። ጊዜው ኢትዮጵያዊነት በራስ ወዳድነት የሚደበዝዝበት ሳይሆን በመስጠት የሚያብብበት ነው። ከመቼውም ጊዜ በላይ አንዳችን ለአንዳችን የምናስፈልግበት ጊዜ ላይ ነን። ወገኔ እየተራብ እኔ ጠግቤ ባድር ሰውነት ምንድነው? ጎረቤቴ ተቸግሮ እኔ ፍሪዳ ጥዬ ለብቻዬ ብደሰት እምነት፣ እውነት ዋጋቸው ስንት ያወጣል?

እንተጋገዝ..ይሄን ክፉ ጊዜ በመተሳሰብ ማለፍ እንጂ ስር በሰደደ ራስ ወዳድነት የምናልፈው አይደለም። ኢትዮጵያዊነት የተገመደበት ተካፍሎ አብሮ የመብላት ባህላችን ሊጎለብት ይገባል። ራስን ከሌሎች ማግለል ስልጣኔ አይደለም። በር ዘግቶ ለብቻ መብላት ዘመናዊነት አይደለም..ዘመናዊነት ነው ብንል እንኳን ኢትዮጵያዊነት አይፈቅድልንም። እኛ ሀበሾች ነን..አብረን በልተን አብረን የምንሞት። ከእውነታችሁ አትውጡ..ከስርዐታችሁ አትሸሹ..አዲሱ ትውልድ ከእናተ የሚማረው ብዙ ነገር አለና እባካችሁ መልካምነትን ተማሩ። ለድሀ ወገናችሁ የምትቆሙበት.. አለኝታነታችሁን የምታሳዩበት ትክክለኛ ጊዜ ላይ ናችሁ። ርህራሄን የምትማሩበት፣ መልካምነትን የምትሹበት ሰሞን ላይ ናችሁ። በዚህ የጭንቅ ወቅት ከመቼውም ጊዜ በላይ ርህራሄአችሁ ያስፈልጋል። በጥቂት ራስ ወዳዶች መልካችን እየወየበ ነው፣ በጥቂት ስግብግብ ነጋዴዎች አንድነታችን እየተሸረሸረ ነው። ወደቀደመ አንድነታችን፣ ወደ ቀደመ ፍቅራችን እንመለስ ዘንድ ከእኔነት መውጣት ግድ ይለናል። ያለዛ ኢትዮጵያ ታዝንባችኋለች..ያለዛ ለተዋቻችሁት ስርዐት በልጆቻችሁ በኩል ዋጋ ትከፍላላችሁ። ይሄ እንዳይሆን ደጋግ ልቦችን የእኛ እናድርግ።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የከተማ ግብርናን በበደሌ ከተማ

**ስምሰም መንግሥቱ**

በተደራጀና በተቀናጀ አሰራር የታገዘ ባይሆንም የጓሮ አትክልት ልማት(የከተማ ግብርና) ለከተሞች አዲስ አይደለም። ለምግብነት የሚውል የአትክልት ልማት በስፋት ባይስተዋልም፣ ለባህላዊ ህክምና የሚያገለግሉ እንደ ጤናአዳም፣ ዳማከሴ፣ ለመአዛነት የሚያገለግሉ እንደ ጠጅ ሳር፣ አርቲ እንዲሁም ለምግብ ማዘጋጃ የሚያገለግሉ እንደ ኮሰረት፣ የጥብስ ቅጠልና የመሳሰሉትን ተክሎች ከደጃፍና ከጓሮ አይጠፉም።

እነዚህን እጽዋት ለልማት የሚውል በቂ መሬት ባይኖርም እንኳ በእቃ እና ባሉት ክፍት ቦታዎች ማልማት የተለመደ ነው። ሰፊ የግብርና ሥራ በሚከናወንበት በገጠርም ሳይቀር ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት አትክልቶች በተጨማሪ ጎመን፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም፣ ድንች የመሳሰሉት አትክልቶች በጓሮ እንዲለሙ ይደረጋል።

የቦታ ጥበትን ምክንያት እያደረጉ ብዙዎች ይህን ልማት እያካሄዱ ባይሆንም፣ ልማቱን የቦታ ጥበት ባለበትም ቦታ ጭምር ማካሄድ የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ ተሞክሮዎች እያመለከቱ ይገኛሉ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በቤተመንግስት አትክልቶችን በማልማት አርአያ ሆነዋል፤ ያለሙትን አትክልትም ሰዎች እንዲጎበኙ በማድረግ፣ ከለማውም በማቋደስ ልማቱ ይበልጥ እንዲሰፋ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል።

የከተማ ግብርና አሁን በመንግስት በኩል የከተማ ግብርና ትኩረት ተሰጥቶታል። ይህን ተከትሎም የተቀዛቀዘው የጓሮ አትክልት ልማት አሁን ሰፋ ባለ መልኩ የከተማ ግብርና በሚል መንግሥትም አቅጣጫ አስቀምጦለት እየተሰራበት ነው። በአዲስ አበባ የከተማ ግብርና በቢሮ ደረጃ እየተመራም ነው። በአዲስ መልክ እየተካሄደ ያለው ይህ የከተማ ግብርና ብዙዎችንም እያነቃቃ ይገኛል።

ለከተማ ግብርና የግድ ሰፊና የተንጣለለ ቦታ አያስፈልግም። በጠባብ ቦታም ልማቱን ማካሄድ ይቻላል። በቂ የልማት ቦታ የሌለው እንኳን ግድግዳንም እንደ መሬት በመጠቀም፣ በየበረንዳውና አጥሩ ጥግ በእቃዎች ጭምር የአትክልት ችግኞችን መትከል ጀምሯል።

የከተማ ግብርና በተለይ የምግብ ዋጋ በናረበት በዚህ ወቅት አስፈላጊነቱ የጎላ ነው። በከተማ ግብርና የሚለሙ አትክልቶች ለምግብነትም ለአይን ማረፊያም በመሆን ያገለግላሉ። ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ የዕለት ፍጆታዎች የሆኑ አትክልትና ፍራፍሬዎች በቀላሉ አልምተው መጠቀም የሚያስችላቸው በመሆኑ አማራጭ የኑሮ ውድነት መፍቻ እርምጃዎች በመሆን የራሳቸው አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፤የአይን ማረፊያ በመሆንም ያገለግላሉ። ለአካባቢ ውበትን ያጎናጽፋሉ፤ ለአልሚዎቻቸውም ትርፍ ጊዜያቸውን ስራ ላይ በማዋል እንዲጠቀሙበት በማድረግ ያገለግላሉ።

የከተማ ግብርና ልማት ጥቅሙ ዘርፈ ብዙ እንደሆነም የዘርፉ ባለሙያዎች ምክራቸውን ሲለግሱ ይሰማሉ። ሰዎች በጓሮአቸው እያለሙ መጠቀምን ባህል እያደረጉ ቢቀጥሉ ተጓጉዞና በተለያየ ሂደት ውስጥ አልፎ ለገበያ ከቀረበው አትክልት ይልቅ ከእርሻ ላይ ትኩስ ማግኘት መቻላቸው ለጤናቸው፣ወጪ በመቆጠብና ድካም በመቀነስ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

በአካባቢያቸው ተደራጅተውና ተቀናጅተው በስፋት ቢያለሙ ደግሞ የገቢ ምንጭ ይሆናቸዋል።ዜጎች ተደራጅተው ሰርተው ገቢ ሲያገኙ መንግሥት ለዜጎች ሥራ ለመፍጠር የሚያደርገውን ጥረት በማገዝ እንዲሁም እንደሀገር በግብርና ሥራ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚደረገውን እንቅስቃሴ በማጠናከር ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

ግልጽና አስተማማኝ የሆነ የከተማ ግብርና ኤክስቴንሽን ሥርአት ቢኖር፣የማህበረሰቡ ትኩረትና ግንዛቤ ከፍ ቢል፣ከታችኛው እርከን እስከ ላይኛው ቅንጅታዊ አሰራር ቢኖር የከተማ ግብርናው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክት እንደሚችል የከተማ ግብርናን አስፈላጊነት አስመልክቶ በተለያየ ጊዜ በተካሄዱ መድረኮች ምክረሀሳቦች ተሰጥተዋል።

እየተነቃቃ ያለው የከተማ ግብርና በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሳይሆን፣በሌሎች የሀገሪቱ ከተሞችም ተሞክሮዎች በመስፋት በመተግበር ላይ ይገኛል። ተቋማት ያሏቸውን ክፍት ቦታዎች ለልማት እንዲውል በመፍቀድ ጭምር እያገዙ የሚገኙበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው።



**በከተማ ግብርና ውጤታማ ለመሆን በጥረት ላይ የሚገኘው የሶዶሚ ጉዲና ቡድን፤**

በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ ዞን በደሌ ከተማ ለሥራ በተገኘንበት ወቅት ተሞክሮውን ለማየት ዕድሉን አግኝተናል። በበደሌ ከተማ ግብርና ጽህፈትቤት ግቢ ውስጥ ተገኝተናል። ለተወገዱ ቁሳቁስ ማጠራቀሚያነት ሲያገለግል የቆየ ቦታ ልማቱ እንዲከናወንበት ተቋሙ ይፈቅዳል። በቦታው ላይ አልምተው ገቢ እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ደግሞ አነስተኛ ገቢ ያላቸው በሴፍቲኔት የታቀፉ ናቸው። ተጠቃሚዎቹም የዳንዲጉዲና ሴፍቲኔት ማህበር አባላት ናቸው።

ማኀበሩ በከተማ ግብርና ልማት ላይ ያለውን ተሳትፎ በተመለከተ የማህበሩ አባል አቶ ተስፋዬ ደምሴ እንደገለጹልን፤ የዳንዲጉዲና ሴፍቲኔት ማህበር 20 ቀጣና ያለው ሲሆን፣እያንዳንዱ ቀጣናም የተደራጁ አባላት አሉት። ከነዚህ ውስጥ አንዱ እርሳቸውን ጨምሮ 32 አባላት የሚገኙበት ቡድን ነው።እርሳቸውም የቡድኑ መሪ(አባ ሶዶሚ) ናቸው።

አባላቱ በከተማ ጽዳት በመንግሥት ተቀጥረው የሚሰሩ ሲሆኑ፣ባላቸው ትርፍ ጊዜ ደግሞ በከተማ ግብርና በመሳተፍ አትክልት አልምተው በመሸጥ በሚያገኙት ኑሮ ገቢያቸውን ይደጉማሉ። የበደሌ ከተማ አስተዳደር በየተቋማቱ ባሉ ክፍት ቦታዎች ሁሉ አልምተው እንዲጠቀሙ ፈቅዶላቸው ነው ወደ ልማት የገቡት።

እኛም በልማቱ ስፍራ ተገኝተን እንዳረጋገጥነው ካሮት፣ ቀይስር፣ ቆስጣና ሌሎች የአትክልት ችግኞችን በአንደኛው መደብ ላይ በማፍላት፣በሌላኛው ወገን ቀድመው ዘር በመበተን ያፀደቋቸውን የተለያዩ የአትክልት አይነቶች ሲንከባከቡ ነበር።

አባላቱ የልማቱን ሥራ ሲያከናውኑ የግብርና ባለሙያዎች ሙያዊ እገዛ ስለሚያደርጉላቸው የሥራ ክፍተት አልተፈጠረባቸውም። አብዛኞቹ አባላት በከተማ ውስጥ የኖሩ በመሆናቸውም እንዲህ ላለው የግብርና ልማት ሥራ ቅርብ አልነበሩም። የግብርና ሥራ የግድ በገጠር ብቻ መከናወን እንዳለበትና ሰፋፊ የሆነ መስኖ ያስፈልጋል የሚል ነበር እምነታቸው።

እያካሄዱ ባሉት ልማት በአነስተኛ ቦታ የተለያየ የአትክልት አይነት ልማት ማከናወን እንደሚቻልም ግንዛቤ አግኝተውበታል። በተግባርም አረጋግጠዋል።ቀድመው ልማቱ ውስጥ አለመግባታቸው ቁጭት ውስጥ ከቷቸዋል። ከልማቱ ገና ጥቅም ባያገኙም ተስፋ አድርገዋል። የልማት ቦታም ሆነ የባለሙያ ድጋፍ እያገኙ ስለሆነ እነርሱም ምርቶቹን ለገበያ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ተጠቀሚ ለመሆን አቅደዋል። የጀመሩት የከተማ ግብርና ከራሳቸው አልፎ ለሀገርም አቅም ይፈጥራል የሚል ተስፋ እንዳላቸው አቶ ተስፋዬ ነግረውናል።

በበደሌ ከተማ እየተከናወነ ስላለው የከተማ ግብርና እና ጽህፈት ቤቱ እያደረገ ስላለው ሙያዊ ድጋፍና ክትትል በተመለከተ የበደሌ ከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት ባለሙያ አቶ ብዙአየሁ ነገሰ እንዳሉት፤ በከተማው የግብርና ሥራ የተጀመረው በ2011ዓም ሲሆን፣ የከተማውን ደረጃ በሚያስጠብቅ መልኩ ነው እየተከናወነ የሚገኘው። የግብርና ሥራውም የሚከናወነው በከተማዋ ዙሪያ ባሉ አካባቢዎች ጭምር ነው። ለተለያዩ የአትክልትና ፍራፍሬ ችግኞች ማዘጋጃ በጽህፈትቤቱ ስር የሚገኝ የችግኝ ጣቢያ በመኖሩ የግብአት አቅርቦት ችግር አያጋጥምም። በሰኔ ወር የሚተከል አቮካዶና ሌሎች ችግኞችንም በማዘጋጀት ለአልሚው ይመቻቻል።

በከተማዋ ለከተማ ግብርና 13 ሄክታር መሬት መዘጋጀቱን አቶ ብዙአየሁ ይገልጻሉ። ከዚህ ውስጥ ወደ 11 ሄክታር የሚሆነው አትክልትና ፍራፍሬ እንደሚለማበት ይገልጻሉ። በቀሪው ሁለቱ ሄክታር ላይ የበቆሎ ልማት ነው የሚከናወነው ይላሉ።

በልማቱ ላይ እንዲሳተፉ ዕድሉ የተመቻቸው ሥራ ለሌላቸው ሲሆን፣እነሱም በማህበር ተደራጅተው እንዲሳተፉ ነው የተደረገው። በዚሁ መሠረትም 42 መሠረታዊ ማህበራት ተደራጅተው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ ሲሉ ያብራራሉ።

ግለሰቦችም በመኖሪያ ቤታቸውና በአካባቢያቸው እንዲያለሙ ይበረታታሉ። አስፈላጊው ድጋፍም በጽህፈትቤቱ ይደረግላቸዋል። ከእርሻ ሥራው ጎን ለጎን ከብት ማድለብ፣ የወተት ልማት፣ዶሮ ማርባት፣ንብ ማነብ በአጠቃላይ ሁለገብ የእንስሳት ልማት በማከናወን በዘርፉ የሥራ እድል እንዲፈጠር ማድረግ ተችሏል።

ሸማቹም ምርቶቹን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ በማድረግ የኑሮ ውድነትን ለማርገብ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ነው አቶ ብዙአየሁ የሚናገሩት። በአካባቢው የከተማ ግብርናን ሰዎች በፍላጎታቸው የሚያከናውኑት እንጂ በተደራጀ መልኩ መንግሥታዊ ድጋፍ እየተደረገለት እንዳልነበር ያስታወሱት ባለሙያው፣ በጽህፈት ቤቱ ክትትልና ድጋፍ በተደራጀ መልኩ መሰራት ከጀመረ ወዲህ የማህበረሰቡም የማልማት ፍላጎት እያደገና ጥቅሙም እየታወቀ መምጣቱን አመልክተዋል። ይህንንም አጠናክሮ በመቀጠል የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

በጽህፈትቤቱ በኩል እየተደረገ ስላለው ሙያዊ ድጋፍና ክትትል አቶ ብዙአየሁ እንዳስረዱት፤ጽህፈት ቤቱ በእንስሳት ልማቱ ላይ የከብቶች አያያዝ፣ጤንነታቸውን እንዴት መከታተል እንዳለባቸው፣አመጋገባቸውን፣በአጠቃላይ ሳይንሱን ተከትለው እርባታውን እንዲያከናውኑ ምክረሀሳብ ይሰጣል፤ አስፈላጊ የሆነ ሙያዊ ድጋፍም ያደርጋል።

አትክልትና ፍራፍሬ ልማቱ ላይም በተመሳሳይ ስለችግኝ ማፍላት፣ችግኞችን በመበተንና ለማጽደቅ መከተል ያለባቸውን ዘዴ በተግባር በማሳየት ጭምር እገዛ ይደረጋል። ግብአትም እንዲያገኙ ከተለያዩ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ይሰራል። ለአብነትም በዶሮ እርባታ ላይ ለተሰማሩ በአካባቢው ከሚገኘው ኤልፎራ ከተባለ ድርጅት የሁለት ቀን ጫጩት እንዲያገኙ ጽህፈት ቤቱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ተሞክሮዎችን ለማስፋትና የልማቱን ተሳታፊዎች ለማበረታታት ሞዴል አልሚዎችን በመለየት እወቅና በመስጠት የማነቃቃት ሥራ ይሰራል።

በዚህም እስካሁን በተከናወነው ሥራ በከብት እርባታና በወተት ልማት ላይ ተሰማርተው ይሰሩ ከነበሩ ማህበራት ሁለት ማህበራትን ወደ ኢንቨስትመንት ደረጃ ማሳደግ ተችሏል። በተለይ በእንስሳት ልማት ለመሰማራት ፍላጎት እያላቸው ነገር ግን በካፒታል(ገንዘብ)እጥረት ችግር ይገጥማቸው ለነበሩ አሁን ላይ ለከተማ ግብርና በተሰጠው ትኩረትና በማህበር ተደራጅተው ለመንቀሳቀስ ፍላጎት ላላቸው ጥሩ መደላድል ተፈጥሮላቸዋል። በእንስሳት ልማቱ ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ቢሟሉ የበለጠ መስራት ይቻላል ያሉት አቶ ብዙአየሁ፣ በተለይ ለእንስሳት ማዳቀያ የሚሆን ግብአት እጥረት መኖሩን ተናግረዋል።

ለከተማ ግብርና ተግዳሮት ከሚሆኑት አንዱ የውሃ አቅርቦት እንደሆነ ይታወቃልና ከዚህ አኳያ የገጠማቸው ችግር ይኖር እንደሆነ አቶ ብዙአየሁ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ በከተማዋ ዙሪያ በሶስት አቅጣጫዎች ከሚፈሱ ወንዞች ተጠቃሚ መሆን የሚቻልበት ዕድል በመኖሩ በዚህ በኩል ስጋቱን ማቃለል ይቻላል።

በደሌ ከተማ አባቦኩና ሹረሙ የተባሉ ቀበሌዎች ያሉት ሲሆን፤አንዱ ቀበሌ 9፣ሌላኛው ደግሞ 8 ቀጣና አለው። በከተማው ወደ አንድ መቶሺ ህዝብ እንደሚኖር ይገመታል።

አጠቃላይ በዞኑ ከተሞች ስላለው የከተማ ግብርና ሥራ የቡኖ በደሌ ዞን ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳዊት ጅፋር እንዳሉት፤ ዞኑ በግብርና ውጤቶች የከተማውን ነዋሪ ፍላጎት የማሟላት ሥራ በቂ እንዳልሆነ በዞን ደረጃ በግምገማ ተለይቶ አቅጣጫ በማስቀመጥ የከተማ ግብርናን የማዘመን ተግባር ለማከናወን ዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው። ግብርናውን የሚያግዙ ባለሙያዎችን በስልጠና ከማብቃት ጀምሮ ነው እርምጃ የተወሰደው።

የልማት የትኩረት አቅጣጫውም የአትክልትና ፍራፍሬ፣እንዲሁም የእንስሳት ልማት መሆናቸውን አቶ ዳዊት ጠቅሰው፣ በነዚህ የልማት ሥራዎች የከተማው ነዋሪ ቢያንስ ራሱን መመገብ እንዳለበት እምነት ተይዞ እየተሰራ ይገኛል ይላሉ። በተለይ በእንስሳት ልማት በኩል በማዳቀል ዘዴ ሰፊ ሥራ መሥራት የሚቻልበት ዕድል በመኖሩ የእንስሳት ተዋጽኦን በበቂ ሁኔታ ለተጠቃሚው ማቅረብ የሚቻልበት እድል እንደሚኖር ኃላፊው አመልክተዋል።

ቢሮው አልተሰራም ብሎ ከገመገመው አንዱ የወተት ማዕከል መቋቋም ላይ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ ዳዊት፣ የወተት ልማቱ ከተከናወነ በኃላ በማእከል የሚቀርብበት ሁኔታ መመቻቸት እንዳለበት መግባባት ላይ ተደርሶ ይህንንም ለማመቻቸት ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመልክተዋል።

በከተሞች በተለያየ ምክንያት ስራ ላይ ያልዋሉ ቦታዎች ሞልተዋል፤ ይህ ብቻ ሳይሆን የተባለው ቦታ ባይኖር እንኳ በእቃ ልማቱን ማካሄድ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ስለመኖራቸው በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤትና በአንዳንድ ቦታዎች የሚታዩ የአትክልት ልማቶች ጥሩ ማሳያዎች ናቸው።

የከተማ ግብርና ልማትን ለማካሄድ በቂ ቦታ የለም የሚል አመለካከት በብዛት ባለበት ሁኔታ በበደሌ ከተማ በከተማ ግብርና በኩል እየተከናወነ ያለው ተግባር እንደ ሀገር ከተያዘው አቅጣጫ ጋር የሚሄድና ለሌሎችም በተሞክሮነት የሚጠቀስ ነው። በተለይ ተቋማት ስራ ላይ ያላዋሏቸውን ቦታዎች ለእዚህ አገልግሎት እንዲያውሉ በበደሌ እየተከናወነ ያለው ተግባር በአርአያነት ሊወሰድ ይገባዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

## ተማሪዎች ነቃ፤ እናቶች እፎይ ያሉበት - የተማሪዎች ምገባ

ጽጌረዳ ጫንያለው

ድህነት ከሚፈትናቸው የዓለም አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ናት። ብዙዎች መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟላት የማይችሉበት ሁኔታ አለ። በተለይም ከመሠረታዊ ፍላጎቶች መሟላት ጋር ተያይዞ የሚያጋጥመው ችግር በቀላሉ የሚታይና የሚፈታ አይደለም። በመሆኑም አሁንም ድረስ ብዙዎች ከመሰረታዊ ፍላጎት በተለይ ምግብ ሲቸገሩ ማስተዋል የተለመደ ሆኗል። በተለይ በአሁኑ ወቅት የኑሮ ውድነቱ ሁሉንም እየፈተነ ባለበት ጊዜ በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኘው ዜጋ ምግብ ፈተና ሆኖበታል። በዚያው ልክ የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት እጅግ ከባድ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ 40 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ የመቀንጨር ችግር እንደሚያጋጥመው ጥናቶች ያመላክታሉ። የምግብ እጥረት ለሰውነትና አእምሮ መቀንጨር ብቻ ሳይሆን ለትምህርት ማቋረጥም አንዱ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል።

ይህንኑ ውስብስብ ችግር ለመፍታት በተለያዩ አካባቢዎች የትምህርት ቤት የተማሪዎች ምገባ እንዲጀመር አስገዳጅ ምክንያት ሆኗል። የምገባ ፕሮግራሙ ከተጀመረ ጀምሮም በተለይ በተማሪዎች ላይ በትምህርት አቀባበል እንዲሁም ከትምህርት ቤት መቅረት ላይ ለውጥ እንዲያመጣ አስችሎታል። ለዚህ ምስክሮቹ የምገባ ፕሮግራሙ ተጠቃሚ ተማሪዎች ናቸው። መምህራንና ወላጆችም ይሄንን ሀሳብ የሚያጠናክሩ ናቸው። በዳግማዊ ምኒልክ አፀደ ሕጻናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተገኝተን ካነጋገርናቸው ተማሪዎች መካከል የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ዳዊት ፍጹም አንዱ ነው። የምገባ ፕሮግራሙ በትምህርቱ ላይ ትኩረት አድርጎ እንዲያጠና እንዳደረገው ይናገራል።

ተማሪ ዳዊት እስከ ስድስተኛ ክፍል ትምህርቱን ሲከታተል በብዙ ችግር እንደነበር ያስታውሳል። በተለይም እናቱን ላለማስቸገር ምሳ ሳይቋጠርለት የሚሄድበት ጊዜ ቀላል አልነበረም። እናቱም ቢሆኑ በሰው ቤት ልብስ አጥበውና ለውዝ ሸጠው ስለሚያስተዳድሩት ሁልጊዜ ሞልቶላቸው ምሳውን ላይቋጥሩለት ይችላሉ። ምግብ ሲኖር ጎርሶ ሲያጣም ረሀቡን ችሎ እንዲማር ተገዷል። ክፍል ውስጥ ቢገባም ትምህርቱን ለመከታተል ግን ይቸገር ነበር። ስለዚህ አብዛኛውን ጊዜ የትምህርቱን ሰዓት በእንቅልፍ እንደሚያሳልፍ ያስታውሳል። ይሄ ውጤቱ ዝቅ እንዲል አድርጎታል።

‹‹እስከ ስድስተኛ ክፍል ግንፍሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው የተማርኩት። በደረጃ ከ20 በላይ እንጂ ከዚያ በታች ወጥቼ አላውቅም›› የሚለው ተማሪ ዳዊት፤ በእናቱ ብርታትና ከእርሱ የባሱ ሰዎችን ሲያይ እንደሚጽናና ይናገራል። ምክንያቱም በረሃብ ምክንያት ራሳቸውን ስተው የሚወድቁ፣ የተማሪዎችን ፊት ላለማየት ከክፍል የሚቀሩ ጥቂቶች እንዳልነበሩ ያስታውሳል።

‹‹የድሃ ልጅ መሆን በትምህርት ቤት ውስጥ በብዙ መልኩ ያሸማቅቃል። ይዞ ከሚመጣው ምግብና መጠን አንጻርም ብዙ ፈተና ነው።›› ያለን ተማሪ ዳዊት፤ አንድ ቀን የገጠመውንና ዘላለም የማይረሳውን ነገር ያነሳል። ጊዜው እናቱ ምሳ ያልቋጠሩለት ነበር። ነገር ግን አብሮ መብላት የተለመደ ስለነበር ያ ጉጉት አድሮበታል። ስለዚህም ከእነርሱ ጋር እመገባለሁ ብሎ አስቦ ትምህርቱን በአግባቡ ተከታትሎ ወጣ። ሆኖም ያሰበው አልሆነም።

ጓደኞቼ ችግሬን ይሸከሙልኛል የሚላቸው ተማሪዎች ምሳ ስላልያዝክ አብረኸን መብላት አትችልም አሉት። በዚህም እጅግ አዘነ። ከእረፍት በኋላ የሆነውን እያሰበ የባሰ ረሃቡ ጠናበት። በዚህም እንቅልፍ ብቻ ሳይሆን እንባም ተናነቀው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከጓደኞቹ ጋር መብላቱን አቋረጠ። ከተቋጠረለት ይበላል ካልተቋጠረ ደግሞ ጦሙን ውሎ ወደቤቱ ይመለሳል። ያን ጊዜ የሆነውን መቼም ማሰብ እንደማይፈልግ አጫውቶናል።

አሁን ነገሮች በመቀየራቸው ደስተኛ ብቻ ሳይሆን በውጤትም የተሻለና የደረጃ ተማሪ እንደሆነ የሚናገረው ዳዊት፤ ይህንን ሥር የሰደደ ችግር በመጠኑም ቢሆን እንደሚቀርፍ ተስፋ የተጣለበት የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም እነርሱን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቻቸውንና መምህራንን እፎይ እንዳስባላቸው ያምናል። በተለይም መንግሥት ወጥ በሆነ መንገድ መተግበሩ ዝቅ ያለ ስሜት ሳይሰማቸው ከእኩዮቻቸው እኩል እንዲማሩና ውጤታማ እንዲሆኑ እንዳስቻላቸውም ያነሳል።



(ፎቶ ጽጌረዳ ጫንያለው)

የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም ተማሪው በትምህርት አቀባበሉና በውጤቱ እንዲሻሻል አስችሏል፤

የትምህርት ቤት የተማሪዎች ምገባ ሰፊ ፕሮግራም እንደሆነና በተለይም ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ትልቅ ሸክምን ያቀለለ እንደሆነ የሚናገሩት ደግሞ በዚሁ ትምህርት ቤት የልዩ ፍላጎት መምህር ሳራ መብራቱ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም ችግረኛ ተማሪዎችን ለመርዳት በትምህርት ቤት ማኅበረሰቡና በተለያዩ ተቋማት ለዓመታት ሲደረግ የነበረ ነው። መምህራንም ድጋፉ አርኪ ባይሆንም ከኪሳቸው እያዋጡ የአቅማቸውን ድጋፍ ያደርጉ ነበር። አሁን ግን በመንግስት ደረጃ ድጋፍ ተደርጎ በወጥነት የምገባ ፕሮግራሙ መጀመሩ ለሁሉም እፎይታን ሰጥቷል።

መምህራኑን ከመዋጮ፤ ተማሪዎቹን ደግሞ ከመሳቀቅ አድኗቸዋል። በዚያ ላይ በትምህርት አቀባበላቸውና በውጤታቸው ጥሩ ደረጃ ላይ እንዲያርፉ እድል ፈጥሮላቸዋል። ከሁሉም በላይ እኩልነት እንዲሰማቸው አድርጓቸዋል። የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም ተማሪዎችን ብቻም ሳይሆን ስራ አጥ የነበሩ የተማሪዎች ወላጆችም የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል። ይሄ በብዙ መልኩ አስደሳች ስራ ነው።

‹‹የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም በመንግስት ደረጃ ሲጀመር ሁሉንም ተማሪ ያካተተ አልነበረም ››የሚሉት መምህርቷ፤ የፕሮግራሙ በጀት ውስን ስለነበረ እንዲመገቡ የሚደረጉት በጣም የተቸገሩትን በመለየት ነበር ። ይህ ደግሞ ተማሪዎች ላይ የሚፈጥረው ጫና ከአሁኑ አንጻር ሲነጻጸር ከባድ ነበር። ምክንያቱም ምሳ አልተቋጠረልኝም፤ አይቋጠርልኝም፤ የድሃ ድሃ ነኝ፤ ርቦኛል የሚል ልጅ ባለመኖሩ ችግረኞችን ለመለየት ይከብዳል። ሲወድቁ አለያም በተማሪዎች አማካኝነት ሲነገረን ብቻ ነው ምዝገባ የምናደርግላቸው። ይህ ደግሞ ችግራቸውን በውስጣቸው ይዘው ውጤታማ ላይሆኑ የሚችሉ ተማሪዎችን ያበራክታል። በዚያ ላይ ተለይተው መታገዛቸው የዝቅተኝነት ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋቸዋል። ስለሆነም የቀደመው እገዛ ጥሩ ጎን እንዳለው ሁሉ ድክመትም እንደነበረበት ያስረዳሉ።

አሁን እየተከናወነ ያለው ግን በብዙ መልኩ ተመራጭ መሆኑን ያነሳሉ። ብዙ እድሎችን ለተማሪዎች ያመቻቸ እንደሆነም ይናገራሉ። በተለይም የማርፈድ ምጣኔ መቀነስ ላይ ያሳዩት ለውጥ እጅጉን ያስገርማቸዋል። በእርግጥ ጠዋት ላይ ቁርስ ይቀርባል። ነገር ግን ብዙ ተማሪ አይመጣም ብዬ አምን ነበር። ሆኖም ያገኘሁት ተቃራኒ ነገር ነው ይላሉ።

በምግብ ምክንያት ትምህርቱን የሚያቋርጥና በክፍል ውስጥ የሚያዛጋ እንዲሁም የሚተኛ ተማሪ የለም። በዚህም የተረጋጋ የመማር ማስተማር ስርዓት ተዘርግቷል። የሁሉም ተማሪ ልዩ ትኩረት ትምህርቱ ላይ ብቻ ሆኗል። በውጤት ደረጃም ብዙ መሻሻሎች ታይተዋል። የመንግስት ትምህርት ቤት ከግሎች ጭምር የተሻለ እንዲሆን አድርጓል ።

በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ዳይሬክተር አቶ ደሊል ከድር በበኩላቸው እንደሚሉት፤ ፍኖተ ካርታው የተማሪዎች የምገባ መርሃ ግብር አለመኖር በትምህርት ጥራት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳርፍ በጥናት ጭምር አረጋግጦ ያስቀምጣል። በመሆኑም የትግበራው መነሻ ይህ ሀሳብ እንዲሆን አስችሏል።

ከተለያዩ ጥናቶች መመልከት እንደተቻለውም ሕጻናት ምግብ ሳያገኙ መማር ስለማይችሉ እንዲያቋርጡ ይገደዳሉ። እናም መጠነ ማቋረጥን ለማስቀረት ምገባ ግድ እንደሆነ ታምኖበት ወደትግበራው ተገብቷል። መጀመሪያ አካባቢ መርሃ ግብሩን ለማስጀመር የተሟላ አሠራር አልነበረም። በዚህም አደረጃጀት በመፍጠር ወይም በዳይሬክተር ጄኔራል ደረጃ በማቋቋም ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል። የአሠራር ሥርዓት ያስፈልግ ስለነበርም ከፍኖተ ካርታውና ከትምህርት ፖሊሲው በመነሳት የማስፈጸሚያ ሥነ ሥርዓትን በማዘጋጀት ጸድቆ ክልል ድረስ እንዲወርድ ተደርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ ደሊል ገለፃ ፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ምርሃ ግብሩ ሙሉ በሙሉ ተጀምሯል። በብዙ መልኩም ለውጦች ታይተዋል። ለምሳሌ፡- መጠነ ማቋረጥን፣ መድገምንና የትምህርት አቀባበልን በብዙ መልኩ አሻሽሏል። በተመሳሳይ ቁጥሩም ቢሆን በብዙ መልኩ ልዩነት ታይቶበታል። ለአብነት መርሃ ግብሩ እንደተጀመረ 25 ሺህ ልጆች የምገባው ተጠቃሚ ነበሩ። በ2014 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ደግሞ ተጠቃሚው 1 ሚሊየን 740 ሺህ 706 ደርሷል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተከናወነ ያለ የምገባ ፕሮግራም በገንዘብ መጠንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ሄዷል። ይህም በመንግስት/ክልሎች በራሳቸው በጀት ብር 2 ቢሊየን679 ሚሊየን 83ሺህ 640፤ በአጋር ድርጅቶች የሚከናወን (WFP, CHILD SFP, ECW & Koica) 415 ሚሊየን122ሺህ 73.32 በድምሩ 3 ቢሊየን 94 ሚሊየን 205 ሺህ 713.32 ብር መያዙንም አብራርተዋል።

በክልል ብዛት እንዲሁም በትምህርት ቤቶች መጠን እየጨመረ እንደሆነ የላኩልን መረጃ ያመላክታል። ይህም የክልል ብዛቱ (ሁለቱን ከተማ አስተዳደሮች ጨምሮ) 9፣ ወረዳ ብዛት 298፣ ትምህርት ቤቶች ብዛት 3,593፣) ናቸው። ያልጀመሩት ደግሞ ቤኒሻንጉል እና ትግራይ ሲሆኑ፤ አሁንም በሀገር ደረጃ ያለው የትምህርት ቤት የምገባ ሽፋን እጅግ ዝቅተኛ መሆኑንም አንስተዋል።

የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም 100 ሺህ ሕፃናትን ሲመገቡ በአማካይ 1ሺህ668 ሰራተኞች ሥራ ይፈጠራሉ ያሉት አቶ ደሊል፤ በአሁኑ ወቅት በ 51 አገሮች ውስጥ ወደ 65ነጥብ 4 ሚሊዮን የሚሆኑ ሕፃናት በአፍሪካ ውስጥ በትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ ናቸው። እ.ኤ.አ. በ 2013 ከነበረው 38ነጥብ4 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር በጣም ከፍተኛ ነው። እናም ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ኢትዮጵያ የምትገኝበት ምስራቅ አፍሪካ 11ነጥብ 4 ሚሊዮኑን እንደሚሸፍን በመረጃው አስቀምጠዋል።

በኢትዮጵያ 16 በመቶ የሚሆነው የተማሪዎች መጠነ መድገም ደግሞ ከተመጣጠነ ምግብ ችግር ጋር የተያያዘ እንደሆነ የሚጠቅሰው መረጃው፤ ይህንን ችግር ለመፍታት ታስቦ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር በሀገር ደረጃ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል ይላሉ።

የተማሪዎች ምገባ አፈጻጸም የተማሪዎች ምገባ መርሃግብር ወደ ተግባር ሲቀየር የክልል ቢሮዎች በራሳቸው በጀትና ከልማት አጋሮች ጋር በተገኘው የገንዘብ ድጋፍ ከቅድመ መደበኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ፤ በ2013 ስኬታማ ከነበሩ እቅዶች መካከል የትምህርት ምገባ መርሃ ግብሩ አንዱ እንደነበር አስታውሰዋል። ምንም እንኳን በአንዳንድ ክልሎች የምገባ መርሃግብሩ አስቀድሞ የነበረ ቢሆንም፤ መርሃግብሩ በ2013 በክልሎች ደረጃ የነበረ አፈጻጸም ጥሩ የሚባል እንደነበረም አብራርተዋል።

በተለይም በኦሮሚያ ክልል፣ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል (በትምህርት ቤት ምገባ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ እና በአንድ ወቅት ተሞክሮውን ማቅረብ የቻለ) እንዲሁም አማራ ክልል በጀት በመመደብ መርሃግበሩን ሲያካሂዱ እንደነበር ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።

የመርሃ ግብሩ መልካም አጋጣሚዎቹ ይህን የምገባ መርሃ ግብር ከተማሪዎች በተጓዳኝ ያመጣው መልካም አጋጣሚ እንዳለ የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ከዚህ ቀደም ልጆቻቸውን ለመመገብ አቅማቸው ይፈተን የነበሩ ወላጆች በዚህ መርሃግብር መጀመር ኢኮኖሚያቸው ከፍ እንዳለላቸው ያስረዳሉ። ምክንያቱም ለቤታቸው ወጪ የሚሆን የልጆቻቸው ወጪ ተቀንሶላቸዋል። እናም በምገባው ብዙ የማህበረሰብ ክፍል እፎይ እንዳለም ይናገራሉ።

በየአካባቢው ከሚገኙ የህብረት ስራ ማህበራት ጋርም የሥራ ትስስር መፈጠሩ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከፍ ያደርገዋልም ብለዋል። እናም የተማሪዎች ምገባ ትኩረት ተሰጥቶ ከተሰራበት የተሻለ እድል ይዞ እንደሚመጣም ያምናሉ። ነገር ግን መንግስት በሰጠው ትኩረት ልክ ማህበረሰቡም ሆነ አጋር አካላት እንዲሁም ተማሪዎች እድሉን በአግባቡ መጠቀምና የተሻለውን ማሳየት ይኖርባቸዋል። ነገሮች መስመር የሚይዙትና የትምህርት ጥራቱ የሚረጋገጠው ሁሉም ክልሎች ለዚህ ሥራ ትኩረት ሰጥተው ሲሰሩ በመሆኑ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃግብሩን በአግባቡ ሊመሩት እንደሚገባም ያሳስባሉ።

# ወቅታዊ

# ‹‹አጣብቂኞች ውስጥ በገባን ጊዜ ሊያሻግር የሚችል ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ በመጠቀም እዚህ ደርሰናል››

**-ፕሮፌሰር አየለ በከሪ የታሪክ ምሁር**

**አስቴር ኤልያስ**

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በቅርስ ጥናት ትምህርት ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር ሆነው ሲሰሩ ነበር። በነበረው ግጭት ምክንያት ግን እዚያ ማስተማሩን መቀጠል አልቻሉም። ይሁንና ስራውን ሳያቋርጡ በተለይ ሦስተኛ ዲግሪ የሚያጠኑትን በማማከር ላይ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ የሀገር መከላከያ ሙዚየም ለመክፈት የያዘው እቅድ በመኖሩ ለዛ የሚሆን ጥናትና ምርምር በማድረግ ላይ ናቸው። በቅርቡም በአሜሪካ ለስድስት ወር ያህል ቆይተው እግረ መንገዳቸውንም ለሙዚየሙ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ይዘው መምጣታቸውን አመልክተዋል። አዲስ ዘመን ከእኚህ የታሪክ ተመራማሪ ከሆኑ ከፕሮፌሰር አየለ በከሪ ጋር ቆይታ አድርጎ እንደሚከተለው አጠናቅሮታል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በታሪኳ የአገር ውስጥ ትንኮሳም ሆነ የውጭ አገር ወረራ ያጋጠማት ሲሆን፤ እርሱንም በድል መወጣቷ ይታመናል፤ በአሁኑ ወቅት በአሸባሪው ቡድን ያጋጠማት ጦርነት ቀደም ሲሉ በአገር ውስጥ ካጋጠማት ትንኮሳ ጋር ሲተያይ እንዴት ይገለጻል ከሚለው ቃል ምልልሳችንን እንጀምር?**

**ፕሮፌሰር አየለ፡-** በጣም ጥሩ፤ ሁሌም ቢሆን ታሪክ ጥሩ መመሪያ ይሰጠናልና ወደ ታሪክ መመለሱ መልካም የሚባል ነው። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለው ጦርነት ለጊዜው ትንሽ ጋብ ቢልም ሁለት ዓመት ያህል የፈጀ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። ይህ ጦርነት ደግሞ የሰው ሕይወት የቀጠፈና በጣም ብዙ ንብረትም ያወደመ ነው። እንዲሁም የአገር ቅርስን ያወደመ በመሆኑ በአገር ውስጥ ከተካሄዱ ጦርነቶች የዚህ አይነቱ ታይቶ የሚታወቅ አይደለም።

አብዛኛውን ጊዜ ተስተውሎ ከሆነ ጦርነቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚቋጩ ናቸው። ደግሞም ብዙዎቹ ጦርነቶች አሸናፊውን ከተሸናፊ የሚለይ ይሆናል እንጂ የሚጓተት አይነት ጦርነት በታሪካችን ውስጥ የለም። ይህ ጦርነት ይበልጥ እንዲጋጋም ነዳጅ የሚያርከፈክፉበት መኖራቸውም እሙን ነው።

ሕወሓት በአገር ውስጥ ከዚህ ቀደም የመከላከያ ሠራዊት የሰሜን እዝን በማጥቃት የመጀመሪያውን ጦርነት ፈጸመ። ሁለተኛው ደግሞ ቀጥታ አዲስ አበባ ለመግባት ያደረገውን ጦርነት በምናስተውልበት ጊዜ የሚደግፈው የውጭ ኃይል ስለመኖሩ አመላካች እንደሆነ ግልጽ ነው።

በሰኔ 2013 ዓ.ም በአገራችን የተካሄደው ምርጫ ህዝቡ በታሪኩ ስርዓት ያለው ህጋዊ መንግስት ያቋቋመበት ነው፤ በተለይም ከዚህ በፊት ያልነበረውንና ህዝቡ ለመጀመሪያ ጊዜ በፈቃዱ ዴሞክራሲያዊ የሆነ መንግስት ያቋቋመ መሆኑ ከግምት ውስጥ ባለማስገባት በውጭ እና በአገር ውስጥ ያለው አካል ዴሞክራሲያዊ የሆነውን መንግስት አፍርሰው ብሎም ህልውናችንን አሳጥተው አዲስ የፖለቲካ ስርዓት ለመገንባት፣ አዲስ የአገዛዝ ስርዓት ለመፍጠር እየተካሄደ የነበረ ጦርነት በመሆኑ ነው ጦርነቱ ረጅም የሆነው።

**አዲስ ዘመን፡-በኢትዮጵያ ውስጥ ተካሂደዋል ከሚባሉ የእርስ በእርስ ጦርነቶች አሁን አሸባሪው ቡድን ካካሄደው ጋር ሲነጻጸር ከጊዜ መርዘም በዘለለ ሌሎቹ ጦርነት የተባሉ አሊያም ግጭቶች ጋር የአሁኑ እንደምን ይገለጻል?**

**ፕሮፌሰር አየለ፡-** እሱን ማየት ካለብን ጥንታዊት እና ዘመናዊት ኢትዮጵያ በሚል ከፋፍለን ነው። በጥንታዊት ኢትዮጵያ የአገዛዝ ስርዓቱ የንግስና ስርዓት ስለሆነ ለረጅም ጊዜ ሚዛኑን ጠብቆ የቆየ ነው። ንጉስ ሊሆን የሚችል ሰው ማን እንደሚሆን የታወቀ ነው። ንጉስ መሆን ያለበት ሰው ማን እንደሆነ የሚያከራክር ቢሆንም እዛው እርስ በእርስ ተከራክረው የሚስማሙበት ሁኔታ ነው የነበረው።

በወቅቱም ህዝቡ ይቃወም የነበረው የንግስና ስርዓቱን አይደለም። እሱን ህዝቡ ተቃውሞም አያውቅም። የቱንም ያህል በመሃላው ሽኩቻዎች ቢኖሩም እርስ በእርስ ስለሚሆን በራሳቸው መንገድ ፈትተው ዘመኑ ወደሚጠይቀው ትክክለኛ መንገድ እንደሚመጡ ነው የሚታወቀው። በዚህ አይነት አካሄድ የንግስና ስርዓቱ ይቀጥላል ማለት ነው። በእርግጥ በዚህ ውስጥ አባት ልጁን እንዲሁም ልጅ አባቱን ለንግስና ሲባል ሊገድል ይችላል፤ በዚህ አይነት መንገድ ነው ኢትዮጵያ እኤአ እስከ 1974 ድረስ የቆየችው።

ይህ በእርግጥ በራሱ የፈጠረው የፖለቲካ መረጋጋት ነበር። በእርግጥ ይህ ስርዓት ኢትዮጵያን አልጠቀመም፤ ጨፍላቂ ነው፤ አሃዳዊ ነው የሚሉም አሉ። ይሁንና በዚህ ስርዓት ውስጥ የረጅም ጊዜ የእርስ በእርስ መባላት የለም። በዚህ ስርዓት ውስጥ የጎጃም፣ የወላይታ፣ የከፋ እና የመሳሰሉ ነገስታትም ነበሩ። በመጨረሻም እነዚህ ነገስታት አንድ ንጉስ የሆኑት ንጉስ አጼ ምኒልክ ነበሩ። በእነዚህ መሃል የተንዛዛ እና ሰፋ ያለ ጦርነት ግን አልነበረም። በእርግጥ ብዙ ግጭቶች ቢኖሩም፤ እነዛ ግጭቶች ቶሎ የሚበርዱ ነበሩ።


ከዚህ አንጻር ሲታይ የአሁኑ ጦርነት በጣም የተለየ ነው። የመጀመሪያው ጉዳይ እርስ በእርስ ነው፤ ሁለተኛ ደግሞ የውጭ ጣልቃ ገብነት አለ። የአሜሪካ ተቋማት የሆኑና ሚዲያዎቻቸው በሙሉ ሁሉም አንድ ላይ ሆነው የኢትዮጵያን ተቀናቃኝ ደግፈው የቆሙበት ጦርነት ነው ማለት ያስደፍራል። በሕወሓት በኩል ለዚሁ ጦርነት ሲባል ህዝቡን አንቀሳቅሰው፣ መስሪያ ቤትና ትምህርት ቤት ዘግተው እንዲሁም መሳሪያ የያዘውንም ሆነ ያልያዘውን አንድ ላይ አድርገው ቀጥታ በማዘመት ተጠምደው ነበር፤ ጉዟቸው የተገታው ደብረ ሲና አካባቢ ነው ማለት ይቻላል።

ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው የአሜሪካ ድጋፍ በመኖሩ ነው። የአሜሪከ ድጋፍ ባይኖር ኖሮ በምንም አይነት ይህን ማድረግ አይችሉም ነበር። በመጀመሪያ ደረጃ ጀርባውን የወጉትን የሰሜን እዝ የአሜሪካ ድጋፍ ባይኖር ኖሮ አያደርጉትም ነበር። እነርሱ ያሰሉት 80 በመቶ መከላከያ ያለው ትግራይ ውስጥ ስለሆነ እሱን ካጠፋንና ከደመሰስነው አራት ኪሎ መግባት ቀላል ነው ብለው ነበር።

የሕወሓት አመራር ለ27 ዓመታት የያዘውን ስልጣን እንደገና መልሶ በእጁ ማስገባት ይፈልጋል። ለዚህ ምክንያት የሚለውም አማራ በድሎናል፤ ገፍቶናል የሚለውም ጭምር ነው። በጥቅሉ በውስጣቸው የአማራ ጥላቻም ስላለባቸው ነው። ራሳቸውን በሚገልጹበት በየትኛውም አጋጣሚ አማራ እንዲህ አድርጎን፤ በድሎን በሚል ትርክት ነው። ከሌላውም ብሄር ጋር ህብረት ለመፍጠር ሲፈልጉም እነርሱ አማራ እንደበደላቸው በመናገር ነው። ለምሳሌ ከኦነግ ሸኔ ጋር የሚያገናቸው ዋና መሰረቱ የሁለታችንም ጠላት አማራ ነው በሚል ስልት ነው። ይህ ግን የፖለቲካ ስልጣኑን ለመጨበጥ እንዲያስችላቸው የሚጠቀሙበት ስልት ነው ብዬ አስባለሁ።

እንዲያም ሆኖ ይህ ሁሉ አካሄዳቸው የትግራይን ህዝብ የሚጎዳ ነው፤ የትግራይ ህዝቦች ራሳቸው አሁን ያላችሁበት ሁኔታ እንዴት ነው ተብለው ቢጠይቁ ፈተና ውስጥ እንዳሉ ነው መናገር የሚችሉት። ሕወሓት ግን ለዚህ መከራ የዳረገህ አማራ ነው ብሎ ነው ሰበብ የሚደረድረው። አመራሮቹ ማንነታቸው የሚገለጸው በራሳቸው ላይ ተመስርቶ አይደለም፤ ‹‹አንተ ማን ነህ?›› ተብለው ቢጠየቁ፤ መልሳቸው ‹‹እኔ አማራ አይደለሁም›› ነው እንጂ፤ ‹‹እኔ ተጋሩ ነኝ፤ ትግራይ ነኝ›› አይደለም። ይህ አሉታዊ ልዕልና በመባል ነው የሚታወቀው።

ሕወሓት ጦርነቱን ለማጋጋም ብሄርን በምክንያትነት አስቀምጠው ያፋጃሉ፤ ብሔር አላዋጣም ካለ ደግሞ ሃይማኖትን መሰረት አድርገው መፋጀት እንዲኖር ያደርጋሉ። ስሜትን የሚያስቆጡ ነገሮች ላይ አጥብቀው ይሰራሉ። ዋና መሰረቱ ግን ያለውን መንግስት አዳክመው በቦታው ለመቀመጥ ነው።



ፎቶ፡ በጸሃይ ንጉሴ

በእርግጥ ስልጣን ከአንዱ ወደሌላ ማለፍ አለበት። ነገር ግን ያ ስልጣን ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሊገምት በሚችል መንገድ ይተላለፍ የሚል ኃይል አለ። በሌላ በኩል ደግሞ የእኛ ታሪክ የሚያሳየን እሱ አይደለም፤ ጠብመንጃ ይዘን በጠብመንጃ እና በጉልበት ስልጣኑን በእጃችን እናደርጋለን የሚል ኃይል ነው ያለው። ሌላው በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያለ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የውጪው ኃይልስ ስምሳሌ አሜሪካ የምትፈልገው ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር አየለ፡-** የውጭው ኃይል በሚታይበት ጊዜ ለምሳሌ አሜሪካ ሃያል ስለሆነች እኛ ደግሞ ያለንበት ጂኦፖለቲካዊ አቀማመጣችን በጣም ጠቃሚ ስለሆነ አሜሪካ በቦታው ላይ የእርሷ የበላይነት እንዲኖር ትፈልጋለች። በዚህ ቦታ ደግሞ ጂቡቲ፣ ሱዳን፣ ሶማሊያ አሉበት። በአካባቢያችን ያሉ አገራት የሚያቋቁሙት መንግስት የአሜሪካ ድጋፍ የሚያስፈልገው አሊያም ከአሜሪካ ጋር ትብብር ሊያደርግ ይገባዋል የሚል አተያይ አሜሪካውያኑ አላቸው።

ምክንያቱም 40 በመቶ የመርከቦች እንቅስቃሴ የሚያልፈው በዚሁ በእኛ ቀጣና ነው። ቦታው በኢኮኖሚም ሆነ ጂኦፖለቲካዊ ጠቀሜታ ያለው ነው። አሜሪካውያኑ በቀጥታ እጃቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ ለማስገባት የቻሉት ሕወሓትን ብቻ መርጠው ከሕወሓት ጋር ሆነው መንግስት ለመገልበጥ የፈለጉበት ዋናው ምክንያት በ2012 ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ሱማሊያ ያደረጉት ስምምነት አለ፤ ይህ ስምምነት በአካባቢያችን ያለውን ሀብት ተባብረን እናልማ፤ ጂኦፖለቲካዊ ጠቀሜታውን ደግሞ ለልዕለ ሃያላኑ መተው የለብንም። እኛም ተጠቃሚ መሆን አለብን። የእኛም ይሁንታ በአካባቢው መኖር አለበት በሚል መስራት መጀመራቸው ነው።

ይህን ግን አሜሪካ የተረጎመችው በሌላ ነው። ይህ አካሄዳችሁ በተለይ ቻይናን እንዲሁም ራሽያን ለመሳብ ነው፤ እኛን ደግሞ ወደጎን ለማድረግ የተሸረበ ጥንስስ ነው ብላ ያን ስምምት ለማፍረስ 24 ሰዓት ሰርታለች። በቅርቡም አንደኛው ድካሚ ውጤታማ ሆኖላታል፤ እርሱም የሱማሊያ ክልል ፕሬዚዳንት የነበሩትን መሀመድ አብዱላሂ ፎርማጆን አውርደው ሐሰን ሼህ መሀመድ እንዲቀመጡ ማድረጋቸው ነው፤ እኚህ ሰው ደግሞ የእነርሱ ሰው ናቸው። እንደሚታወቀው ጂቡቲ ላይ ካሉ የውጭ ጦር ትልቁ የአሜሪካ ነው። በዚያ አካባቢ ከአምስት ሺህ በላይ ጦር አላቸው። በዚያ ስፍራ አሜሪካንን ጨምሮ ቻይና፣ ጃፓን፣ ፈረንሳይ ጣሊያን በጥቅሉ የሌለ የለም ማለት ያስደፍራል።

ስለዚህም ነው እነ ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ሱማሊያ ባደረጉት ህብረት ጂቡቲ ያለመካተቷ ምስጢር። ጂቡቲ በጥቅሉ በሚባል ደረጃ ከቁጥጥር ውጪ በመሆኗ ነው በቡድኑ ውስጥ ያላስገቧት። ምክንያቱም ሉዓላዊነቷን ከጥያቄ ውስጥ እንዳስገባች የምትቆጠር አገር ሆናለችና ነው። አሜሪካ ደግሞ ዒላማ ያደረገቻቸው ሶስቱን አገራት ነው።

የሱማሊያ ነገር አሁን ላይ ውስብስብ ነው፤ ለምን ቢባል አዲሱ የሱማሊያ ፕሬዚዳንት ሼህ ሀሰን ከሕወሓት ጋር ይሰሩ ነበር። የእርሳቸው መመረጥ ያስደሰታቸውም ለዚህ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንዴት?**

**ፕሮፌሰር አየለ፡-** ምክንያት ካልን 327 የፓርላማ

# ወቅታዊ

አባላት ብቻ መርጦ የሰጠው ምርጫ ነው። ህዝቡ ድምጽ አልሰጠም። እነዚህ ድምጽ የሰጡት የፓርላማ አባላት ድምጻቸውን የሰጡት አውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ድንኳን ተጥሎላቸው ነው። በተጨማሪም ምርጫውን ያካሄዱት ከአፍሪካ በተወጣጡ የጸጥታ ሃይሎችና በታንክ ተከበው ነው። የፓርላማ አባላቱን የወከላቸው ጎሳው መርጧቸው ነው እንጂ ህዝቡ መርጧቸው አለመሆኑም ልብ የሚባል ነው። ዋናው ነጥብ 327 ሰው ብቻ ድምጽ ሲሰጥ 327ቱ የጎሳ ውክልና ስላላቸው ወይ በአልቃይዳ አሊያም በአሜሪካ ወይም ደግሞ በአውሮፓ ኅብረት በቀጥታ ተጽዕኖ ስር ሆነው ሊገዙ ይችላሉ የሚለው ነው።

ነገር ግን በዚህ ሁሉ መሃል ማየት ያለብን ነገር በሶማሊያ ውስጥ አንደኛ ስጋት የሆነው አልሻባብ ነው። ሼህ ሐሰን፣ ቀደም ሲል ፕሬዚዳንት በነበሩበት ጊዜ ከአልሻባብ ጋር ተዋግተዋል። እኤአ በ2012 እስከ 2016 ስርዓት ያለው የፖለቲካ አካሄድ የሚባለው ነገር የተጀመረውም በእርሳቸው አገዛዝ ዘመን ነበር። አሁንም ቢሆን አልሻባብ ዓላማው ኢስላሚክ መንግስትን መመስረት ነው። ይህንንም መመስረት የሚፈልገው በሶማሊያ ብቻ ተወስኖ ሳይሆን በቀጣናው ሁሉ ነው። ይህ የአልሻባብ ስርዓት ለሼህ ሀሰንም፣ ለፎርማጆም ሆነ ለኢትዮጵያም አይጠቅምም። ይህ ደግሞ የጋራ የሆነ ነገር ይፈጥራል። አሜሪካንን ልብ ብልሽ እንደሆነ ሰውዬው በተመረጠ ማግስት ወደ ሶማሊያ 500 ወታደር እንደገና ልካለሁ አለች፤ የመላካቸውም ምስጢር አልሻባብን ለመዋጋት ለሚደረገው ሂደት ድጋፍ ለማድረግ ነው።

በእርግጥ አሜሪካ ኢትዮጵያ ውስጥ ያላት ተጽዕኖ ገና ሙሉ በሙሉ እነርሱን በሚያረካ መልኩ አይደለም። አሜሪካ የምትፈልገው ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ መንግስት ከቻይና ወይም ከራሺያ ወይም ደግሞ ከአውሮፓ ህብረት ያለው ተጽዕኖ ከእኛ መብለጥ የለበትም፤ መምራት ያለብን እኛ ነን የሚል ነው። ይህ በሌላ አገላለጽ ኢትዮጵያን በቅኝ አገዛዝ ውስጥ ማድረግ ነው። ፍላጎታቸው የእነርሱ አገልጋይ መንግስት ማድረግ ነው። ያንን ሊያደርግልን የሚችለው ሕወሓት ነው እንጂ ብልጽግና አይደለም ብለው ደምድመዋል።

ባለፈው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ለፓርላማ ሲናገሩ የተደመጡት ከአሜሪካ ጋር ያለን ተግባቦት ጥሩ ነው በሚል ነው፤ ያስቸገረን ኮንግረንሱ ነው ብለዋል። ይሁንና ኮንግረንሱ ለብቻው ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆን አይችልም። በተለይ የውጭ ጉዳይን በሚመለከት ውሳኔው የኋይት ሃውስ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግስት ከኋይት ጋር ያለውን ግንኙነት እያሻሻለ እስከሄደ ድረስ ችግር የለውም።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ሱማሊያ መካከል የተደረገው ስምምነት የአሜሪካ ከሕወሓት ጋር ባላት ትስስር የተነሳ ምን ያህል ጫና ውስጥ ይወድቃል?**

**ፕሮፌሰር አየለ፡-** እንዳጋጣሚ ሆኖ ያንን ውል ሲያደርጉ የተፈራረሙት መሪዎቹ ብቻ ናቸው። ወደሕዝቡ ዘንድ እንዲሁም ፓርላማም አልደረሰም። በእርግጥ ኢትዮጵያና ኤርትራ ውሉን ወደጎን የሚያደርጉበት ምንም ምክንያት የላቸውም። እንዲያውም አሜሪካ ተጽዕኖዋን በጣም በምታበረታበት ጊዜ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነቷን ታጠናክራለች የሚል እምነት ነው ያለኝ። ምክንያቱም አንደኛ ከራሽያ ጋር ውል ተፈራርመዋል። ሁለተኛ ደግሞ አሁን ባለው የፖለቲካ ሁኔታ ኤርትራ እንደበፊቱ ለብቻዋ ልትቀመጥ አትፈልግም።

**አዲስ ዘመን፡- ሕወሓት ጦርነት ለመጀመር ነጋሪት እየጎሰመ ስለመሆኑ ይነገራል፤ ይህ አካሄዱ በህዝብ ስም መነገዱን አመላካች ነው እንጂ ከበባው ወይም ድጋፍ ማጣቱ ብቻ አይመስልምና እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር አየለ፡-** ሕወሓትን ወደ ጦርነት እንዲገባ የገፋፋው አንዱ አሜሪካ ድጋፍ ስላሳየችው ነው። አሜሪካንን የሚያክል ኃይል የሚደግፈው ከሆነ መኪና እርዳታ ይዞ አልገባም ይላሉ፤ መድሃኒት አልቀረበም ሲሉ ያማርራሉ። ከዚህ ሌላ እኛ በማናውቀው ቴክኖሎጂ አማካይነት ደግሞ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ። ስለዚህ ከበባውም ድጋፍ ማጣቱም አይመስለኝም።



ከበባው ሐሰት ነው። በህዝብ መካከል ምንም ጥላቻ የለም። እነርሱ የፈጠሩት ችግር እንጂ። በመሆኑም ከበባ ያሉት ከእውነት የራቀ ነው። ከዚህ በፊት መከላከያ መቀሌ ሲገባ የተቋረጠውን መብራት፣ ውሃና መሰል አገልግሎት ለማስተካከል በተገኙ ባለሙያዎች ላይ በተለይ ከመቶ በላይ የሆኑ የኤሌክትሪክ ሠራተኞች ተገድለዋል። የቴሌም ሆነ የውሃ ክፍል ሠራተኞች ተገድለዋል።

በእርግጥ አሁን አሁን ሕዝቡ አመራሩ የራሱን ስልጣን ለማስቀጠል ደፋ ቀና ማለቱን እየተረዳ መጥቷል። አመራሩ ደግሞ ዓላማው መንግስትን ደካማ በማድረግ ቦታውን ለመያዝ ነው። ሕወሓት የአሜሪካ አገልጋይ ሆኗል። አሜሪካም ከፊት ከፊት ሆና እየረዳችው ነው። የአሜሪካንም ዓላማ ሕወሓት የሚባል ድርጅት ወይ ኢትዮጵያ እንዲበታተን አሊያም ስልጣኑን ይዞ የእነርሱ ተላላኪ እንዲሆን ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ አሜሪካንን አልፈልግም ብሎ አልተወም፤ ከአንዱ ጋር ብቻ መለጠፉን ስላልመረጠ ቻይናንም ራሽያንም ቀርቦ እየሰራ ነው። አልሻባብን ለመውጋት ከአሜሪካ ጋር ይተባበራል። ለሕወሓት ግን ጦርነት ለማካሄድ እውነተኛ የሆነ ምክንያት መኖር አለበትና የእርሱ ምክንያት ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አልተገኘም። ጦርነት አፍራሽ መሆኑን በአግባቡ የተረዳ አይመስለኝም፤ ይልቁንም የሕወሓትን ስግብግብነት ነው የሚያሳየው። ከአሜሪካ በሚሊዮንና በቢሊዮን የሚቆጠረውን ብር ነው ያዩት እንጂ ጦርነት የሚያስከትለውን ፈተና አልተረዱትም።

ሕወሓት በአንደኛው እና በሁለተኛው ጦርነት አልተሳካለትም፤ እንደገና ግን ለሶስተኛ ጦርነት እየተዘጋጀ ነው፤ ይህን ሲያደርግ ህዝቡ አሁንም መከራ ውስጥ መኖሩን እያወቀ ነው። ይህ የሚያሳየው በፊትም ቢሆን ሲያሳድዱ የነበረው የራሳቸውን ጥቅም ነው፤ አሁንም እያደረጉ ያለው ይህን ነው ማለት ይቻላል። ለሕወሓት ጥፋት አሜሪካ ደግሞ ተጠያቂ መሆን አለባት፤ ምክንያቱም አሜሪካ ባታበረታታቸው ኖሮ የዚያን ያህል ጥፋት ለማጥፋት ችሎታው አይኖርም ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ማን ነው አሜሪካንን ጥፋተኛ ነሽ ሲሳት የሚችለው?**

**ፕሮፌሰር አየለ፡-** ልዕለ ኃያል ናት በሚል ብቻ ጥፋተኛ ነሽ ላትባል አትችልም። ሌላው ቢቀር የሰራቻቸውን ጥፋቶች በሰነድ መልክ ታሪክ እንዲያወሳው ጠቅሶ ማለፍ ግድ ይላል። በቅርቡ ያስተዋልነው ጉዳይ አለ። ሲነኳቸው እሪ የሚሉ አውሮፓውያኑም ሆኑ ሌሎች፤ ራሺያና ዩክሬን ወደጦርነት ሲገቡ የኃይል ሚዛናቸው ምን ያህል ውስን እንደሆነ ለማየት በቅተናል።

እነርሱ ለመኮርኮም የሚቺኩሉት እንደኛ ገና በማደግ ላይ ያሉ አገሮችን ነው። አሁን ግን የዩክሬንና የራሽያ ጦርነት በመኖሩ ትንሽ ፋታ ሰጥቶን ሰንብተናል የሚል እምነት አለኝ። ሕወሓትም ምቹ ሁኔታን የመጠቀም የቀደመ ልምድ ያለው እንደመሆኑ አሁንም የሕዝቡን ረሃብ መሰረት አድርጎ ነው ለጦርነት ሲደራጅ የሚስተዋለው። መኪና ወደመቀሌ እንዳይገባ የማድረጉ ምስጢር ሁሉንም ነገር እኛ መቆጣጠር አለብን ከሚል የመነጨ ነው።

በእርግጥ ቀደም ሲል መበደሉና መዋረዱ ምርር ብሏቸው ወደትግል የገቡ እውነተኛ ታጋዮች እንደነበሩ የሚካድ አይደለም። የሕዝቡ ጥያቄ የእኔም ጥያቄ ነው በሚል ወደትግል የገቡ እንደነበሩ ይታወቃል። በዚህም ብዙ መስዋዕትነት የከፈሉ ታጋዮች ነበሩ። ነገር ግን አሁን እሱ ግንባር ራሱን ትራንስፎርም አድርጎ የጥቂቶች መጠቀሚያ ሆኗል። ለዚህም ነው አመራሩ ሊያሸንፈው ወደማይችለው ጦርነት ውስጥ ለመግባት የሚቋምጠው። ዋና ግቡም ራሱን የመጀመሪያ ተጠቃሚ ለማድረግ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ይህ ቡድን የትኛውንም የተቀደሰ ቦታ ሆነ መሰረተ ልማትንና ቅርሶችን ማጥፋት ዓላማው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የሚስተዋል የድንበር ውዝግብ መኖሩ ይታወቃል፤ ይህ ከአሸባሪው ቡድን ጋር አንዳች የተያያዘ ነገር እንዳለ ያመላክት ይሆን?**

**ፕሮፌሰር አየለ፡-** እርግጠኛ ነኝ ሱዳን ይህን የድንበር መግፋት ሁኔታዋን ካላቆመች በእሳት እንደመጫወት ነው የሚቆጠርባት። አንደኛ የእኛን መሬት ነጥቀዋል፤ የነጠቁት ደግሞ እኛ ጦርነት ላይ ሆነን ነው። ይህን ጊዜ ያሰሉት እነርሱን ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው በሚችል ሁኔታ ነው። ሁለተኛው ስሌታቸው እኛን ተንኩሰውን የአገር ውስጡን ጦርነት ትተን ወደእነርሱ ፊታችንን እንድናዞርና ሕወሓት አራት ኪሎ እንዲገባም ጭምር ነበር። በወቅቱ መንግስት የወሰነው ውሳኔ ትክክል ነው። ጉዳዩ ምንም እንኳ ከበድ ያለ ቢሆንም በዚህ ስሜታዊ ሆኖ ወዳልተገባ ተግባር አለመግባቱ በሳልነቱን የሚሳይ ነው። ነገር ግን መሬቱን እኛ በምንፈልግበት ጊዜ የግድ የምናስመልሰው ይሆናል። ሱዳንና ሕወሓት የሚያደርጉት ቅንጅት ደግሞ የአሜሪካንን ፖሊሲ ለማራመድ ነው። አሜሪካም ብትሆን ፍላጎቷ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በሚሊታሪ ጥገኛ አገር ሆና እንድትቀጥል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ እያራመደች ያለውን ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ እንዴት ያዩታል?**

**ፕሮፌሰር አየለ፡-** የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ደካማ ነው፤ ትልቁ ክፍተታችን እዛ ላይ ነው የሚለውን ሐሳብ አልጋራም፤ አልስማማበትም። ለምሳሌ በጣም ባለብሩህ አዕምሮ የሆኑ በግል የማውቃቸው ዲፕሎማቶች አሉን። ታሪካችንም የሚያሳየው ይህንኑ ነው።

በጣም የሚያስገርመውን ነገር ላስታውስሽ፤ እንደባለፉት ጊዜያት አንዲትን በማደግ ላይ ያለችንና ወደ እድገት ጎዳና የገባችን አገር በመቃረን የተቆመበት ጊዜ የለም ብዬ በድፍረት መናገር እችላለሁ። እኔ በየቀኑ በዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ሲነገሩና ሲሰበኩ የነበሩ ጉዳዮችን ዝርዝር ይዣለሁ። ለምሳሌ ኒዮርክ ታይምስ ኢትዮጵያን በተመለከተ በየቀኑ አርቲክል ያወጣ ነበር። አልጀዚራም ሆነ ሌሎቹ ሁሉ እንዲሁ ሲያደርጉ ነበር።

ከሚዲያዎቹ በተጨማሪ ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም አይነት ጥላቻ የሌላቸው አገሮች እንዲሁ ከኢትዮጵያ በተጻራሪ ቆመዋል። እንደ አየርላንድ፣ ፊንላንድ ሌላው ቀርቶ ዩክሬን፣ ኢስቶኒያ አይነት ሃገሮች ሁሉ እንዲሁ ነበሩ። ሌላው ቀርቶ በጣም ቅርባችን ናቸው የምንላቸውና እዚሁ ቤተክርስቲያን ያላቸው እነ አርሚኒያ በሙሉ ከአሜሪካ ጎን ቆመዋል። ሀገራችን እንድትበታተን ሁሉም የየራሳቸውን ሚና ተጫውተዋል።

ይህ ሁሉ ጫና ኢትዮጵያ ላይ ሆኖ አገራችን ግን ይህንን የከፋ ጊዜ በጥበብ ከመወጣት በላይ ምን አይነት ዲፕሎማሲ ነው ያለው። ሌላው ቀርቶ በህዳሴ ግድባችን ላይ የነበረውን ጫና ጥበብ በተሞላበት ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ ማለፍ መቻልን የመሰለ ነገር ምን አለ። የተለያዩ አጣብቂኞች ውስጥ በገባን ጊዜ ሁሉ እንደየጉዳዩ አይነት በበቂ ሁኔታ ሊያሻግር የሚችል ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ በመጠቀም እዚህ ደርሰናል። ስለዚህ በእነርሱ አካሄድ ቢሆን ኖሮ ፍርክስክሳችን ይወጣ ነበር፤ ግን አልሆነም፤ ያልሆነው ደግሞ ዲፕሎማሲያዊ አካሄዳችን ተሽሎ በመገኘቱም ጭምር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ፕሮፌሰር ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ፕሮፌሰር አየለ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## የሩሲያ ሠራዊት የዩክሬንን ስትራቴጂያዊ ከተማ ሊማንን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ

አዲስ አበባ፡ የሩሲያ ጦር ስትራቴጂያዊ ፋይዳዋ ከፍተኛ ነው የተባለችውንና ምስራቃዊቷን የዩክሬን ከተማ ሊማንን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠሩን አረጋገጠ፡፡

የሩስያ ጦር በዩክሬን ምሥራቃዊ ክፍል ዶንባስ ክልል የሚያደርገውን የማጥቃት ዘመቻ አጠናክሮ በመቀጠል የሊማን ከተማ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር ማዋሉን የሀገሪቱ የመከላከያ ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡

በሌላ በኩል የሩሲያ ጦር ወደ ስሎቪንስክ የሚያደረገውን ግስጋሴ የዩክሬን ተከላካይ ኃይሎች እንደገቱት የሚያመላክት መረጃ በዩክሬን በኩል ወጥቶ እንደነበር ዘገባው አስታውሷል፡፡

በዩክሬን ሉሃንስክ ግዛት ወደ 10 ሺህ የሚጠጉ የሩሲያ ወታደሮች መሠማራታቸውን የዩክሬን ምሥራቃዊ ክልል አስተዳዳሪ መናገራቸውን በዘገባው ተጠቅሷል፡፡

የዩክሬን ጦር በመከላከል እና የሩሲያ ኃይሎች ደግሞ የሊማን ከተማ ለመቆጣጠር ለብዙ ቀናት ብርቱ ውጊያ ሲያደርጉ መቆየታቸውንም የቲአርቲ ዘገባ ያመለክታል፡፡

የዩክሬን ፕሬዚዳንት ቭላዲሚር ዘለንስኪ የሩስያ ጦር የኢንዱስትሪ ተቋማት ማዕከል በሆነው በዶንባስ ክልል



የሚያደርገው ውጊያ እየከፋ በመምጣቱ ምዕራባውያን አገራት የጦር መሣሪያ ድጋፋቸውን እንዲያጠናክሩ ጥሪ አቅርበዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሩሲያ ሃይፐርሶኒክ ዚርኮን ክሪዝ የተባለ ሚሳኤል በተሳካ ሁኔታ ማስወንጨፏን የሀገሪቱ የመከላከያ ሚኒስቴር በዛሬው ዕለት ይፋ አድርገዋል።

የሚሳኤል ሙከራው የተካሄደው በአርክቲክ ባሬንትስ ባህር ውስጥ ሲሆን፥ በአንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ርቀት የሚገኘውን ዒላማ በተሳካ ሁኔታ መምታቱን የሚኒስቴሩ መግለጫ ጠቁሟል፡፡

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ተምዘግዝገው ዒላማቸውን የመምታት አቅም ያላቸው አዳዲስ ሚሳኤሎች በቅርብ ጊዜ ውስጥ በውጊያ ግዳጅ ላይ እንደሚሰማሩ መናገራቸው ይታወሳል፡፡

ከሳምንት በፊት የሩሲያ ወታደሮች ከኪየቭ ቀጥላ ትልቋን ሁለተኛ ከተማ፥ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታዋ ከፍተኛ የሆነችውንና የዩክሬን የወደብ ከተማ ማሪዮፖልን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠራቸው ይታወሳል።

ከተማዋን ለመቆጣጠርም ለአንድ ወር ያህል ሁለቱ ወገኖች ሕይወትም ንብረትም ያወደመ ፍልሚያ ማካሄዳቸው ተመላክቷል ፡፡

በተለይም በማሪዮፖል ከተማ አቅራቢያ በሚገኘው አዞቭስታል የተሰኘው የብረት ፋብሪካ ውስጥ መሽገው ሲዋጉ የቆዩ 531 የዩክሬን የመጨረሻ ወታደሮች ለሩሲያ እጅ ለመስጠት ተገድደዋል።

የዩክሬን ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ዘለንስኪ በአዞቭስታል የብረት ፋብሪካ የሩሲያን ጦር ሲመክቱ የነበሩ የአገራቸው ወታደሮች ስፍራውን ለቀው እንዲወጡ ትዕዛዝ ሰጥተው እንደነበርም ሞስኮ ታይምስ በዘገባው ማስፈሩ ይታወሳል፡፡

## በአሜሪካ ቴክሳስ በአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች እና መምህራን ላይ የተፈጸመው ግድያ ቁጣ አስነሳ

አዲስ አበባ፡ በአሜሪካ ቴክሳስ ግዛት በአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ 19 ተማሪዎች እና ሁለት መምህራን ላይ የተፈጸመው ጅምላ ግድያ በሕዝብ ዘንድ ቁጣና የተቃውሞ ሰልፍ ማስነሳቱ ተገልጿል።

ሰልፈኞቹ በጥይት የተገደሉ ተማሪዎችን ፎቶግራፎች ይዘው "ብሔራዊ የጠብመንጃ ማኅበርን አንፈልግም"፣ "የተገደሉት ልጆቻችሁ ቢሆኑ ኖሮስ " የሚሉ እና ሌሎች መሰል ይዘት ያላቸው መፈክሮችን ይዘው ተቃውሟቸውን አሰምተዋል፡፡

ቴክሳስ ግዛት በምትገኘው ዩቫልዴ በተሰኘችው ትንሽ ከተማ ውስጥ በሚገኝ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በ 18 ዓመቱ ወጣት የተፈጸመው ግድያ "ኤ አር 15" በተሰኘ ከፊል አውቶማቲክ ጠብመንጃ የተፈጸመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን በነገው ዕለት በሚኖረው መርሐ ግብር ጅምላ ግድያ በተፈጸመበት ትምህርት ቤት ተገኝተው የሟቾችን ቤተሰቦች እንደሚያጽናኑ ተነግሯል፡፡

በጉዳዩ ላይ የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ በሰጡት አስተያየት፥ ለተፈጸመው ጥቃት ዴሞክራቶችን ተጠያቂ አድርገዋል፡፡

የትምህርት ቤቶች የደኅንነት ሁኔታ በድጋሚ እንዲጤንና ከመሰል አደጋዎች እንዲጠበቁም የጠየቁት ትራምፕ፥ በሀገሪቷ ያለው የአዕምሮ ጤና አጠባበቅ እና ክትትል ሁኔታ መጤን እንዳለበትም አሳስበዋል፡፡

መምህራን ሥልጠና አግኝተው ወደ ክፍል በድብቅ የሚገቡ የጦር መሳሪያዎችን መያዝ እንዲችሉ መፈቀድ እንዳለበት ዶናልድ ትራምፕ መናገራቸውንም ሲጂቲ ኤን ዘግቧል፡፡

ሪፐብሊካኗ የደቡብ ዳኮታ ገዢ ክርስቲ ኖኤም፣ ተቃዋሚዎቹ ከመሣሪያ ቁጥጥር ጋር በተያያዘ የሚያደርጉትን ትግል እንዳያቆሙ ያሳሰቡ ሲሆን ፤ ሪፐብሊካኑ የቴክሳስ ገዢ ግሬግ አቦት በትዕይንተ ሕዝቡ ላይ በመገኘት ለሟች ቤተሰቦች ኃዘናቸውን እንደገለጹ ተመላክቷል፡፡

በሌላ በኩል የተቃውሞ ትዕይንተ-ሕዝቡ በሚካሄድበት አቅራቢያ ባለ ሕንጻ ውስጥ ፤ የጅምላ ግድያው ከተፈጸመ




ከሦስት ቀናት በኋላ ፣ የአሜሪካው ብሔራዊ የጠብመንጃ ማኅበር ዓመታዊ ስብሰባውን እያካሄደ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር**
**በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

# የንጽሕና መጠበቂያ ስርጭት ለሴት ተማሪዎች

የወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያ እጦት ሴት ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው ከሚያስቀሩ ምክንያቶች አንዱ ነው። ምናልባትም ይህ ችግር ከከተማ ይልቅ በገጠሩ አካባቢ ጎልቶ ሊታይ እንደሚችል እሙን ነው። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የአቅም ማጣት እና የተደራሽነት ችግር ናቸው። በዚህም ሳቢያ ተማሪዎቹ ከትምህርት ገበታቸው ከመቅረት በተጨማሪም እስከማቋረጥ ይደርሳሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤ ከሴት ተማሪዎች ንጽህና መጠበቂያ ስርጭት ጋር በተያያዘ ባሳለፍነው ግንቦት 11 ቀን 2014 ዓ.ም ባዘጋጀው መድረክ ላይ ተሞክሯቸውን ካካፈሉት መካከል የእቴጌ መነን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሴት ተማሪዎች ተጠቃሽ ናቸው።

ተማሪዎቹም ትምህርት ቤታቸው አስር ፍሬ የሚይዝ በወር ሁለት እሽግ የንጽህና መጠበቂያ (ፓድ) እንደሚሰጣቸውና እጥረት እንደማያጋጥማቸው ይናገራሉ። ሁሉም ትምህርት ቤቶች ለሴት ተማሪዎች እንደ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት የንጽሕና መጠበቂያ መስጠትና የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መሥራት እንዳለበትም ይገልፃሉ።

ዶክተር ሀና የሺ ንጉስ የአዲስ አበባ ሴቶች ህፃናት እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ናቸው። እርሳቸው እንዳሉት፤ ለሴት ተማሪዎች የንጽህና መጠበቂያ አቅርቦት ማመቻቸት የተማሪዎችን ውጤት የሚያሳድግ ነው፤ ከተማ አስተዳደሩ የትምህርት



**ዶክተር ሀና የሺ ንጉስ የአዲስ አበባ ሴቶች ሕፃናት እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ**

ጥራትን ለማስጠበቅና የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል ምገባን ጨምሮ የተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ፣ ለሴት ተማሪዎች የንፅህና መጠበቂያ እንዲሁም ለበርካታ ሴቶች በትምህርት ቤት ምገባ የሥራ እድል ተፈጥሮላቸው ወደ ተግባር ተገብቷል።

በተለይ ከሴት ተማሪዎች የንፅህና መጠበቂያ ጋር ተያይዞ ስርጭቱ ላይ ክፍተት መኖሩን በዳሰሳ ጥናት ማረጋገጥ መቻሉን የተናገሩት ዶክተር ሀና፤ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ (ሞዴስ) ገዝተው መጠቀም የማይችሉ ሴት ተማሪዎች ዑደቱን ጠብቆ በየወሩ በሚመጣ የወር አበባ ምክንያት በየወሩ ቢያንስ ከአራት እስከ አምስት ቀናት ከትምህርት ገበታቸው ይቀራሉ። ይህም በዓመት በአማካኝ ከ40 እስከ 50 ቀናት በመሆኑ በውጤታቸው ላይም ሆነ በትምህርት ተሳትፏቸው ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራል።

የቢሮው ምክትል ኃላፊና የሴቶች ዘርፍ ኃላፊ ወይዘሮ ሜሮን አራጋው በበኩላቸው፤ ቢሯቸው ከምገባ ኤጀንሲ ጋር በጋራ ባደረገው የዳሰሳ ጥናት የሴት ተማሪዎች የንፅህና መጠበቂያ በአግባቡ እየተሰራጨ ባለመሆኑ የሴት ተማሪዎች ውጤት መቀነስ እንዳሳየ ያመለክታሉ።

በአዲስ አበባ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬ ክተርና የጥናት ቡድኑ ሰብሳቢ አቶ መለሰ ድንቁ ያቀረቡትን ጥናት ዋቢ አድርገው እንደገለፁት ፤ በወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያ እጦት ምክንያት በርካታ ሴቶች ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ። በራስ መተማመናቸው ከመቀነሱ በተጨማሪ ራሳቸውን የሚያገሉበት ሁኔታም አለ። ተማሪዎቹ ትኩረት የሚሰጡት ከወር አበባ ጋር ተያይዞ ለሚገጥማቸው ችግር እንጂ ለትምህርት ባለመሆኑ በክፍል ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ እንዲቀንስ የሚያደርግ በመሆኑም በትምህርታቸው ውጤታማም አይሆኑም። በተጨማሪም ተማሪዎቹ ትምህርት አቋርጠው ያለ አስተማሪ ፈቃድ ከክፍል ውስጥ ይወጣሉ። በአጠቃላይ በወር አበባ ምክንያት አንዲት ሴት ተማሪ በወር ከአንድ እስከ አራት ቀን ትቀራለች ። ይሄ በዓመት ሲሰላ ከ22 እስከ 40 ቀን ይደርሳል። በመሆኑም ጥናቱ እነዚህንና ሌሎች ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ ለሁሉም ለመንግስት ትምህርት ቤት ሴት ተማሪዎች የወር አበባ ንፅሕና መጠበቂያ በጀት ተይዞለት መስጠት አስፈላጊ ነው። እንደሌሎቹ ሁሉ በግዢ ስርዓቱ በጀት ሊያዝለት ይገባል።

የምገባ ኤጀንሲ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ መተግበር ሲገባው ያልተገበረው የሴት ተማሪዎች የንፅህና መጠበቂያ ስርጭት ነው ያሉት የምገባ ኤጀንሲ ኃላፊ ወይዘሪት አንቺነሽ ተስፋዬ፤ ኤጀንሲው ከተቋቋመ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ስድስት የምገባ ማዕከል በማቋቋም ከአስር ሺ በላይ የዕለት ጉርስ የሌላቸውን ዜጎችን በመመገብ፣ ለ628 ሺ ለሚሆኑ ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት በመስጠት እና ለ799 ሺ ተማሪዎች የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) እና የትምህርት ቁሳቁስ ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየሠራ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ወይዘሪት አንቺነሽ በማከል ኤጀንሲው የበጀት እጥረት ፣የተደራሽነት እና የወቅታዊነት ችግር ያለበት በመሆኑ፤ በቀጣይ ኤጀንሲው የተጣለበትን ኃላፊነት እንደሚወጣም መግለጻቸውን ከአዲስ አበባ ሴቶች ህፃናት እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ማህበራዊ ትስስር ገጽ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# ስፖርት

## የኦሊምፒክ ለዛና ጣዕም፣ በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ስቴድየም

**ቦጋስ አበበ**

ታላቁን የስፖርት መድረክ ኦሊምፒክ ከሌሎች ታላላቅ የስፖርት መድረኮች ለየት የሚያደርገው ነገር የመክፈቻና የመዝጊያ ሥነሥርዓቱ ነው። ኢትዮጵያ በተለያዩ ዓመታት በኦሊምፒክ ጽንሰ ሃሳብ መሠረት በርካታ አገር አቀፍ ውድድሮችን ለማከናወን ጥረት አድርጋለች። ትናንት ለመጀመሪያ ጊዜ በሐዋሳ የተጀመረውን የኢትዮጵያ ወጣቶች ኦሊምፒክን የመሰለ የመክፈቻ ሥነሥርዓቱ በኦሊምፒክ ለዛና ጣዕም የተዋጀ ውድድር ግን ማስታወስ አስቸጋሪ ነው። ድንገት የጣለው ዝናብ ሳይረብሻቸው የመክፈቻው ሥነሥርዓት ድምቀት ከሆኑት ከኢትዮጵያ አየር ኃይል ሄሊኮፕተሮች አጀብ አንስቶ እስከ ሲዳማ ፈረሰኞችና በአጭር ዝግጅት የተለያዩ ትርኢቶችን በማራኪ ሁኔታ እስካቀረቡት ወጣቶች የመክፈቻ ሥነሥርዓቱ በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ስቴድየም የተዋጣ ሆኗል።

ይህ የመክፈቻ ሥነሥርዓት ኦሊምፒክ ኦሊምፒክ በሚሸቱ ትርኢቶች ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ እንግዶችም የታጀበ ነበር። የታላቁ የኢትዮጵያ የኦሊምፒክ ጀግና አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ታሪካዊ ተፎካካሪ የኬንያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት አትሌት ፖል ቴርጋት እስከ አፍሪካ ኦሊምፒክ ኮሚቴዎች ማኅበር ዋና ጸሐፊ አሕመድ ሃሺምና ሌሎችም ዓለም አቀፍ እንግዶች እንዲሁም የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በሥነ ሥርዓቱ ታድመዋል።

የውድድሩን መጀመር በስፍራው ተገኝተው ያበሰሩት የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አገኘው ተሻገር፣ ጽንሰ ሃሳቡ በዓለም ላይ ከሰረጸ መቶ ዓመታትን የተሻገረው ኦሊምፒክ ሰላም የሰፈነባት የተሻለች ዓለምን



አስተናጋጁ የሲዳማ ክልል በአጭር ጊዜ ዝግጅት ደማቅ የመክፈቻ ሥነሥርዓት በማሳየቱ ተመስግኗል፣

ለመፍጠር፣ በፍትሐዊ ውድድር መግባባትን፣ከመሸናነፍ በላይ ተሳትፎን የሚያስቀድም መሆኑን በማስታወስ ሁሉን በአንድ ላይ በሚያሰባስበው መድረክ ወጣቶችን በስፖርት ማሰባሰብ ጥቅሙ ከስፖርትም የበለጠ መሆኑን ተናግረዋል። “ኦሊምፒክ ለኢትዮጵያ የአልሸነፍ ባይነት ምልክት ነው” ያሉት አፈ ጉባኤው የአበበ ቢቂላ የሮም ኦሊምፒክ ድል ለዚህ ማሳያ መሆኑን አንስተዋል። ኦሊምፒክና ኢትዮጵያ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸውን ከአበበ ቢቂላ በኋላ በታላቁ መድረክ ድል የተቀዳጁ በርካታ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ማሳየታቸውን ያስታወሱት አፈ ጉባኤው በትውልድ ቅብብሎሽ የደመቀውን የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ቀጣይነት ለማረጋገጥ የወጣቶች ኦሊምፒክ መካሄዱ ያለውን ፋይዳ አብራርተዋል። በዚህ መድረክ ወጣቶችን በተገቢው ዕድሜ በማወዳደርም በዋናው ኦሊምፒክ ሀገርን የሚወክሉ አትሌቶች የሚፈሩበት መሆን እንደሚገባው አስገንዝበዋል። በውድድሩ የሁለት ሳምንት ቆይታ የኦሊምፒክን ጽንሰ ሃሳቦች ተግባራዊ በማድረግ ተወዳዳሪዎች በመተሳሰብና በሰላም እንዲያጠናቅቁ አሳስበዋል።

የውድድሩ አስተናጋጅ ሲዳማ ክልል ፕሬዚዳንት ደስታ ሌዳሞ ባደረጉት ንግግር፣ የኦሊምፒክ ጽንሰ ሃሳብ ካለ አንዳች ልዩነት በአንድነትና በመተሳሰብ አብሮ የመኖር ጥበብ መሆኑን በማስታወስ የኦሊምፒክ ዓላማና ግብ ለአሁኗ ኢትዮጵያ ትልቅ መልዕክት እንዳለው ገልጸዋል። “ወንድማማችነትና ኅብረትን ከኦሊምፒክ መማር አለብን” ያሉት ፕሬዚዳንቱ ኦሊምፒክ ወጣቶች ከራስ ይልቅ ለሀገር ቅድሚያ መስጠትን የሚማሩበት መድረክ መሆኑን በመገንዘብ በዚህ መድረክ የሚሳተፉ ወጣቶች ሊኮሩ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በክብር እንግድነት የተገኙት የአኖካ ዋና ጸሐፊ አሕመድ ሐሺም በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ትልቅ የኦሊምፒክ አቅም እንዳላቸው በመግለጽ ያላቸውን እምቅ አቅም በእንዲህ አይነት መድረኮች አውጥተው መጠቀም እንዳለባቸው ጠቁመዋል። ከዚህም ባሻገር በዚህ የወጣቶች ኦሊምፒክ ኢትዮጵያውያን አንድነታቸውን ለዓለም ሕዝብ ማሳየት እንዳለባቸው በማስገንዘብ አፍሪካውያን ምሳሌ አድርገው እንዲመለከቷቸው ማድረግ እንደሚገባ አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት ዶክተር አሸብር ወልደጊዮርጊስ ባደረጉት ንግግርም፣ እየቀነሰ የመጣውን የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ውጤት ለማሻሻል ትምህርት ቤቶችን የተተኪ ስፖርተኞች መፍለቂያ በማድረግ በወጣቶች ኦሊምፒክ መድረክ እንዲያልፉ ጥረት መደረግ እንዳለበት ገልጸዋል። ይህ የወጣቶች ኦሊምፒክ ኢትዮጵያ መልካም ገጽታዋን የምታስተዋውቅበትና የሚወራባት አሉባልታ እውነት እንዳልሆነ ለዓለም የምታሳይበት አጋጣሚ እንደሚፈጥርም አክለዋል። አንድነትና መተባበር ምን ያህል እንደሚያጠናክርም ወጣቶች ከዚህ መድረክ እንደሚማሩ ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

እስከ ሰኔ 04/2014 በሚቆየው በዚህ የወጣቶች ኦሊምፒክ ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተውጣጡ ስድስት ሺ ያህል ወጣቶች በኦሊምፒክና የኦሊምፒክ ባልሆኑ ስፖርቶች ተሳታፊ ናቸው። ከኦሊምፒክ ስፖርቶች አትሌቲክስ፣ እግር ኳስ፣መረብ ኳስ፣ ቅርጫት ኳስ፣ እጅ ኳስ፣ ብስክሌት፣ ቦክስ፣ጅምናስቲክና ወርልድ ቴኳንዶ ፉክክር የሚደረግባቸው የስፖርት አይነቶች ሲሆኑ የኦሊምፒክ ባልሆኑ ስፖርቶች ቼዝ፣ ኢንተርናሽናል ቴኳንዶና ውሹ መካተታቸው ታውቋል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ጤና መምሪያ ሞቲቴ ፉራ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በ2014 ዓ.ም ለተለያዩ

አገልግሎት የሚውል የተለያዩ ዕቃዎችን አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

**በዚህ መሰረት፡-**

ሎት 1. የመድሃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ

ሎት 2. የደንብ ልብሶች

በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡

1. ተጫራቾች በመስኩ የ2014 ዓም የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው እንዲሁም የዘመኑን ግብር የከፈሉ እና ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ሰርተፍኬት እና የታክስ ከፋይነት ቲን ቁጥር ሊኖራቸው ይገባል፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 300 (ሶስት መቶ ብር) በመክፈል ዘወትር በስራ ሰዓት በሞቲቴ ፉራ መጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በፈለቀች ሆቴል በኮብልስቶኑ ገባ ብሎ በሚገኘው ሆስፒታል 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 42 ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 (አስር) የስራ ቀናት እሁድ እና ቅዳሜን ሳይጨምር ከጠዋቱ 2:30 እስከ 11:30 ከምሳ ሰዓት ውጪ ሰነድ መግዛት ይችላል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ከሎት-1 እስከ ሎት-2 ላለው ህጋዊ ከሆነው በባንክ በተረጋገጠ ብር 10,000 (አስር ሺ ብር) ሲፒኦ በጥሬ ማስያዝ ግዴታ አለባቸው፡፡
5. ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቡትን ሰነድ ዋናውን (ፋይናንሽያል) እና ፎቶ ኮፒውን (ቴክኒካል) ሰነዶችን ለየብቻ በታሸጉ ፖስታ በማሸግ ከላይ በተጠቀሰው ቀን እና ቢሮ ለዚህ ጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡
6. ጨረታው የሚከፈተው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ11ኛው ቀን ከቀኑ 8:30 ሰዓት ታሽጎ በዕለቱ 9:00 ሰዓት ይከፈታል፡፡
7. የጨረታው አሸናፊ የሆነው አቅራቢ ድርጅት ዕቃዎችን በራሱ ትራንስፖርት ሆስፒታል ድረስ በማምጣት የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
8. ሆስፒታሉ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 0462200046 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ጤና መምሪያ ሞቲቴ**

**ፉራ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል**



## የሥራ ቅጥር ማስታወቂያ

ድርጅታችን ደመራ ኢንጂነሪንግ እና ኮንስትራክሽን ከዚህ በታች በተጠቀሱት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ በኮንትራት ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የስራ መደብ መጠሪያ | ብዛት | ደሞዝ | ተፈላጊ ችሎታ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የትምህርት ደረጃ | የስራ ቦታ | የስራ ልምድ |
| 1 | ፕሮጀክት መሀንዲስ | 01 | በስምምነት | በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ማኔጅመንት ትምህርት ሙያ ወይም ቢ.ኤ.ሲ ዲግሪ ሲቪል መሀንዲስ ወይም በተመሳሳይ ሙያ | ፕሮጀክት ሳይት | ከ8 ዓመት በላይ |
| | | 02 | በስምምነት | በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ማኔጅመንት ትምህርት ሙያ ወይም ቢ.ኤ.ሲ ዲግሪ ሲቪል መሀንዲስ/ የውሃ ወይም የኢሪጌሽን መሃንዲስ ወይም በተመሳሳይ ሙያና ልምድ | ፕሮጀክት ሳይት | ከ8 ዓመት በላይ Waste Water Treatment Plant ላይ የሰራ |
| 2 | ሳይት መሀንዲስ | 04 | በስምምነት | በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ማኔጅመንት ትምህርት ሙያ ወይም ቢ.ኤ.ሲ ዲግሪ ሲቪል መሀንዲስ | ፕሮጀክት ሳይት | ከ6 ዓመት በላይ |
| 3 | የቢሮ መሀንዲስ | 02 | በስምምነት | በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ማኔጅመንት ትምህርት ሙያ ወይም ቢ.ኤ.ሲ ዲግሪ ሲቪል መሀንዲስ | ፕሮጀክት ሳይት | ከ6 ዓመት በላይ |
| 4 | ኮንስትራክሽን ፎርማን | 03 | በስምምነት | አድቫንስ ዲፕሎማ ህንጻ ቴክኖሎጂ | ፕሮጀክት ሳይት | ከ10 ዓመት በላይ |
| 5 | የቅየሳ መሀንዲስ | 01 | በስምምነት | ዲፕሎማ በሰርቪይንግ | ፕሮጀክት ሳይት | ከ6 ዓመት በላይ |
| 6 | ጠቅላላ አገልግሎት | 01 | በስምምነት | 12ተኛ የጨረሰ | አዲስ አበባ | 0 ዓመት |

ማሳሰቢያ፡-

* ለስራ መደቡ የተጠቀሰው ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ ስለሆነ ከተወሰነው ተፈላጊ ችሎታ በላይ --ያለው እንዲወዳደሩ ይበረታታል፡፡
* የተጠቀሰው ተፈላጊ ችሎታ የምታሟሉ ተወዳዳሪዎች አንድ ጉርድ ፎቶግራፍ፣ የትምህርት እና የስራ ልምድ ማስረጃዎችን ዋናውንና ከማይመለስ አንድ ግራፍ ፎቶ ኮፒ ጋር በማቅረብ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ከ05 እስከ 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ከታች በተጠቀሰው አድራሻ በአካል በመቅረብ ማመልከት የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡፡

አድራሻ፡- ጠመንጃ ያዥ ቴሌ ጋራዥ ፊት ለፊት የኋላ ወርቅ ህንጻ ንብ ባንክ ያለበት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 4 ስልክ ቁጥር፡ - 0114 67 04 88

**ደመራ ኢንጂነሪንግ እና ኮንስትራክሽን**